የኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ
Ethiopian Cities Association

ስማርት የከተማ እንቅስቃሴ ስርዓት (SMART URBAN MOBILITY SYSTEM) መልካም ተሞክሮ ሰነድ

በኢትዮጵያ ከተሞች
የትብብር መድረክ የተዘጋጀ

2017 ዓ.ም

www.ethiopiancities.org

ABOUT ETHIOPIAN CITIES ASSOCIATION (ECA)

The Ethiopian Cities Association (ECA) is an alliance of currently 106 Ethiopian cities working towards improving the living conditions of the urban Ethiopian population. ECA was established in February 2009, during the first Ethiopian Cities Day event.

It is a voluntary membership organization owned by and accountable to its members. The ECA aspires for all Ethiopian cities to be prosperous, sustainable, productive, and competitive.

The formation of ECA is the joint interest and effort of Ethiopian Cities to strengthen coordination of their efforts and mutually work towards mitigating the deep-rooted and diversified urban problems in their cities.

Ethiopian Cities Association was registered and licensed to operate as a consortium of Ethiopian Resident Society in accordance with the Charities and Societies proclamation no. 621/2009 on March 25, 2011 and secured its certificate bearing number 2228.

The number of ECA's members has also grown from 19 cities at the time of its establishment to 106 cities.

To be an association of cities that can add value for the making of livable, sustainable, productive and competitive Ethiopian cities.

- Support cities in achieving their mission, complying with principles of good governance and decentralization,
- Serving as a platform of experience exchange for cities,
- Identifying and disseminating best practices to cities,
- Promoting and facilitating sister city twinning,
- Creating network of cooperation with governmental and non-governmental bodies for cities
- Working to make member cities internationally competitive Core Values
- Excellence
- Professionalism
- Innovative
- Independence
- Teamwork
- Inclusiveness
- Dynamic

UNITING LOCAL GOVERNMENTS IN ETHIOPIA (ULGE)

ስማርት የከተማ እንቅስቃሴ ስርዓት
(SMART URBAN MOBILITY SYSTEM)
መልካም ተሞክሮ ሰነድ



ሀዳር 2017 ዓ.ም
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

ስማርት የከተማ እንቅስቃሴ ስርዓት
(SMART URBAN MOBILITY SYSTEM)
መልካም ተሞክሮ ሰነድ

የመጀመሪያ ዕትም

ህዳር 2017 ዓ.ም

ህዳር 2017 ዓ.ም
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

©መብቱ በኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ የተጠበቀ ነው::

ህዳር 2017 ዓ.ም
አዲስ አበባ

ህዳር 2017 ዓ.ም
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

ማዉጫ

መግቢያ 5

ክፍል አንድ፡- አጠቃላይ ሁኔታ 8

1.1. የሀገሪቱ ብዛት እና አደረጃጀት 8

1.2. አቅጣጫ 9

1.3. ኢኮኖሚ 10

1.4. የሄግ ከተማ መስህቦች በከፊል 12

1.5. የሄግ ከተማ አስተዳደር ሀገነጸ እና ሎጎ 19

1.6. የመንግስት መቀመጫ (Seat of Government) 21

1.7. የመናገሻ ከተማ (Royal City) 22

1.8. ብዝሀነትን የምታስተናግድ ከተማ (Diverse City) 22

1.9. ሜትሮፖሊታን ከተማ (Metropolitan City) 23

1.10. ሄግ በተማሪዎች ተመራጭ ከተማ (Student City) 24

1.11. አዶ ዴንሃግ ስቴዲየም 25

1.12. ሄግ የቱሪስት መዳረሻ ከተማ (Tourist Friendly City) 26

1.13. ሄግ የሰላም እና የፍትህ ማዕከል (The Hague as a Hub for Peace and Justice) 27

1.14. የመንግስታት ትብብር እና ያልተማከለ አስተዳደር (Intergovernmental Cooperation and Decentralization) 27

ክፍል ሁለት፡- የሄግ ከተማ ዘላቂ የትራንስፖርት መሠረተ ልማት እና አገልግሎት 32

2.1. በሄግ ከተማ ዋና ዋና የመጓጓዣ ዘዴዎች 32

2.1.1. የሀዝብ ትራንስፖርት 32

2.1.2. የግል የመጓጓዣ ዓይነቶች 39

2.1.3. የጋራ ተንቀሳቃሽነት አማራጮች (Shared Mobility Options) 44

2.2. የተቀናጀ የመጓጓዣ አውታር (Integrated Transportation Network) 52

ክፍል 3፡- የተወሰዱ ዋና ዋና ትምህርቶች 56

ማጠቃለያዎች 58

የዋና ዳይሬክተሩ መልዕክት



የኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ ሀገራችን ውስጥ በሚገኙ ከተሞች በጎ ፈቃድ አማካኝነት በ2003 ዓ.ም የተመሠረተና ተጠያቂነቱም ለአባላቱ የሆነ ፤ ለትርፍ ያልተቋቋመና መንግሰታዊ ያልሆነ ድርጅት ነው። ድርጅታችን አሁን ላይ 106 ከተሞችን በአባልነት አቅፎ የያዘ ሲሆን ከተሜነትን በማስፋፋትና የነዋሪዎችን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል በሚደረገው ጥረት የበኩልን አስተዋጽኦ እያበረከተ ይኛል።

ተቋማችን ከተመሠረተበት ጊዜ አንስቶ የከተማ ልማት ዘርፍን በሚመለከት የመሥክነሪያ፣ የእውቀት ሽግግርና የመሳባቢያ መድረክ በመሆን በአባል ከተሞች ውስጥ በተለያዩ እርከን የሚገኙ አስተዳደሮች ተልዕኳቸው በብቃት ለመወጣት በሚያደርጉት እንቅስቃሴ የተሳካ እንዲሆን በማገዝ ላይ ይገኛል።

ይህም ሆኖ የኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ ላለፉት ዓመታት በርካታ ውጣ ውረዶችንም ያሳለፈ ቢሆንም ካለፉት 5 ዓመት ወዲህ ግን ማህበሩ ባደረገው መሰረታዊ የመዋቅር ለውጥ በርካታ አመርቂ ውጤቶችን አስመዝግቧል።

በተለይም ለአባል ከተሞች እየሰጣቸው የሚገኙ ቀልጣፋ፣ ዘመናዊና ጥራታቸውን የጠበቁ አገልግሎቶች የማህበሩን ገጽታ፣ ክብርና ዝና የበለጠ እንዲጎለብት መንገድ ጠርገውሊታል። ይህንኑም ተግባር በማጠናከር በተለያዩ የኢትዮጵያ ከተሞች የተለያዩ መድረኮችን በማዘጋጀትና የእውቀት ሽግግር በማድረግና አንዱ ከተማ ከሌላኛው ትምህርት እንዲቀስም መድረክ በማመቻቸት በከተማ ልማት ዘርፍ እድገት ዙሪያ የራሱን አሻራ በማሳረፍ ላይ ይኛል። በሃገር ውስጥ ብቻ ላይገደብ የውጪ ሃገራትን ተሞክሮዎች በመቀመርና የጉብኝት ፕሮግራም በማዘጋጀት አባል ከተሞቹ የተሻለ ልምድ እንዲያገኙ መንገድ አመቻችቷል፣ ወደፊትም ይህንኑ ተግባር አጠናክሮ ይቀጥላል።

በተለይም ከተሞቻችን በተለያዩ ዘርፎች ስማርት በመሆን ለነዋሪዎቻቸው ምቹና አካታች እንዲሆኑ ትብብር መድረክ ቀን ከሌት እየሰራ እንደሚገኝ ስናዝር በኩራት ነው። በመሆኑም ከተሞቻችንን ስማርት የማድረግ ስራ ተጠናክሮ ይቀጥል ዘንድ ይህ የተሞክሮ ሰነድ በርካታ ቁምነገሮችን የያዘ በመሆኑ እንድታነቡት ስጋብዘችሁ በደስታ ነው።

መልካም ንባብ!!

አቶ እንዳሻለም ጤናው ሃብቴ
የኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ
ዋና ዳይሬክተር

መግቢያ

ከተሞቻችን በፍጥነት እያደጉ ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ ደህንነቱ የተጠበቀ፣ አመቺ እና ሁሉንም የህበረተሰብ ከፍሎች የሚያካትት የመኖሪያ አካባቢ መፍጠር እና የተቀላጠፈ የትራንስፖርት አገልግሎት ማቅረብ አስፈላጊ ነው። ለረዥም ጊዜ የከተሞቻችን የትራንስፖርት አቅድ አቅጣጫ የአብላጫውን በአግር የሚንቀሳቀሱ፣ ሳይክል ወይም የህዝብ ትራንስፖርት የሚጠቀሙ የማህበረሰብ ከፍሎችን ባለማማከል፣ የግል ተሽከርካሪዎች ፍላጎት ላይ ትኩረት አድርጎ ሲሰራ ቆይቷል። ይህ አቅጣጫ የተሽከርካሪ መጨናነቅን እና የመንገድ ደህንነት ከመፍጠሩም በላይ በዚህ ምክንያት በኢኮኖሚ አድጎት፣ በምርታማነትና በህዝብ ጤና ላይ ችግርን ሲያስከትል ቆይቷል። ይህንን ተከትሎ የአገራችን የትራንስፖርት እና የአየር ንብረት ፖሊሲዎችን እና ስትራቴጂዎችን መነሻ በማድረግ ሞኮር አልባ እንቅስቃሴን ለማበረታታት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፊር ቀዳጅነት በርካታ የትብብር መድረኩ ዓባል ከተሞች የኮሪደር ልማት ትግበራ ላይ ይገኛሉ።

ትብብር መድረኩ ይሄንን ታሳቢ በማድረግ በኮሪደር ልማት ሙሉ በሙሉ ወደተግባር ያልገቡ የተመረጡ ከተማ ከንቲባዎችን በዘላቂ የከተማ ትራንስፖርት አገልግሎት እና መሰረተ ልማት፣ በሞኮር አልባ እንቅስቃሴ እንዲሁም በትራንስፖርት ስራአመራር የውጭ አገር ልምድ እንዲያገኙ አድርጓል። በዘላቂ ከተማ ትራንስፖርት አገልግሎት ለተሻለ ተሞክሮንት የተመረጡቸዋ አገር እና ከተማ የአዘርላንድ ሄግ ከተማ ስትሆን ከተማዋ ያስመዘገበችው የዘላቂ ትራንስፖርት የአገልግሎት አሰጣጥ ተጨባጭ ውጤት ለተሻለ ተሞክሮንት የሚያበቃት ነው። ከአዘርላንድ አገር ሄግ ከተማ በዘላቂ የትራንስፖርት አገልግሎት እና መሠረተ ልማት ዝርጋታ የተገኙ አዳዲስ እውቀቶች እና ልምዶች በዚህ ሰነድ ውስጥ በዝርዝር ቀርበዋል።

በድኑ የተሻለ ተሞክሮ ለማግኘት የሚመለከታቸው የሄግ ከተማ አመራሮችንና ባለሙያዎችን እንዲሁም የዘርፉ ልዩ ልዩ ተዋናዮች በገለጻዎች፣ በጉብኝቶች፣ መረጃዎችን በፎቶ ግራፍና ቪዲዮ አማካይነት በመቅረጽ፣ የተለያዩ ዶክመንቶችን በማሰባሰብ ልምዶችን የወሰደ ሲሆን ለሀገራችን ይጠቅማሉ ያላቸውን ተሞክሮዎች በዚህ ሰነድ ውስጥ በስፋት እንዲካተቱ ተደርጓል።

ሰነዱ የከተማዋን የሰነ ሕዝብ አወቃቀር፣ ኢኮኖሚ፣ አስተዳደር እና ዘላቂ የትራንስፖርት አገልግሎትና መሠረተ ልማቶችን በዝርዝር ይዳስሳል። ወደ 570,000 የሚጠጋ ህዝብ ብዛት ያላት ሄግ ኢኮኖሚዋ በብዙ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች፣ የኮርፖሬት ዋና መሥሪያ ቤት እና ቱሪዝም ዘርፍ ተጠናክሯል። ሰነዱ የመንግስታት ትብብርን አስፈላጊነትን በመዳሰስ ሄግ የአለም አቀፍ ህግ እና ፍትህ ማዕከል በመሆን የተለያዩ አለም አቀፍ ድርጅቶችን እንደምታስተናግድ ያብራራል። እንደ ማዱሮዳም፣ ቬቨኒንገን የባህር ዳርቻ እና የሰላም ቤተ መንግስት ያሉ ቁልፍ መስህቦች የከተማዋን ማራኪነት በማጎልበት ለቱሪስት ምቹ መዳረሻ አድርጓታል።

ሰነዱ ከተማዋ ያልተማከለ አስተዳደርን ለማስፈን በሚደረገው ጥረት እና የህብረተሰቡን የአስተዳደር ተሳትፎ በተመለከተ ዝርዝር ጉዳዮችን ዳሰሳ አድርጓል። ሄግ ከተማ ኤችቲኤም የተሰኘ መንግስታዊ ተቋም የሚተዳደር እና ለዘላቂ ትራንስፖርት ትኩረት የሰጠ የተቀናጀ የህዝብ ማመላለሻ ስርዓት ባለቤት ናት። ከተማዋ የብስክሌት ተጠቃሚዎችን ለማበረታታት ቨርካታ የብስክሌት መስመሮችን እና የብስክሌት ማቆሚያ ስፍራዎች ዘርግታለች።

የዚህ ሰነድ አላማ የኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ የሄግ ከተማን በከተማ የዘላቂ ትራንስፖርት ዙሪያ ትምህርት በመውሰድ ለአገራችን ከተሞች በሚስማማ መልኩ ቀምሮ ለማስፋት ነው።

ክፍል አንድ፡- አጠቃላይ ሁኔታ

፲.፲ የህዝብ ብዛት እና አደረጃጀት

ሄግ ከተማ በኔዘርላንድ አገር ከሚገኙ ከተሞች አንዷ ስትሆን ከአምስተርዳም እና ከሮተርዳም ከተሞች በመቀጠል በህዝብ ብዛት ሶስተኛዋ ትልቋ ከተማ ነች፡፡ በሄግ ከተማ ወደ 570,000 የሚገመቱ ነዋሪዎች የሚኖሩ ሲሆን የሀገሪቱ አስተዳደር ዋና ከተማ በመሆን በማገልገል ላይ ትገኛለች፡፡ ከተማዋ 2.7 ሚሊየን ህዝብ የሚኖርበት የሮተርዳም-ሄግ ሜትሮፖሊታን አካል ስትሆን ሜትሮፖሊታን አካባቢው ሮተርዳም፣ ሄግ እና ሌሎች 21 ከተሞችን ያቀፈ እና ስፋቱም 1,130 ስኩዌር ኪ.ሜ ነው፡፡ እ.ኤ.አ. በ2014 የተመሰረተው ይህ ሜትሮፖሊታን አካባቢ በስፋቱ ከኔዘርላንድ ሦስ እንዲሁም ከአውሮፓ 10ኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ በሄግ በአውሮፓ ትልቁ ወደብ የሚገኝባት ከተማ ናት፡፡ (Eurostat, 2023)

ከተማዋ በ8 ክፍለ ከተሞች (districts) የተከፋፈለች ሲሆን ከፍለከተሞቹም በጥሱ 44 ሰፈሮችን (Neighbourhood) ይዘዋል፡፡ ከፍለከተሞቹም ሴንትረም፣ ኢስካምፕ፣ ሃግስ ሀውት፣ ላክ፣ ላይደሸንዪን-የፔንበርግ፣ ሎሰዱይንን፣ ቬቨኒንገን እና ሲንበርክ በመባል ይታወቃሉ፡፡ ሄግ በከተማዋ ምክር ቤት እና በክንቲባ የምትተዳደር ሲሆን የአሁኑ ክንቲባ ጃን ቫን ዛነን (Jan van Zanen) በመባል ይታወቃል፡፡ የሄግ ማዘጋጃ ቤት የከተማ ፕላንን፣ የህዝብ አገልግሎቶችን እና የአካባቢ ፖሊሲ ማውጣትን ጨምሮ የተለያዩ ተግባራትን በሀላፊነት እያከናወነ ይገኛል፡፡



ፎቶ ፲፡- የሄግ ከተማ ስምንቱ ከፍለ ከተሞችን የሚያሳይ ካርታ



ፎቶ 2፡- ከቡር ጃን ቫን ዛነን የወቅቱ የአለም የከተሞች ማህበር ፕሬዚዳንት እና የሄግ ከተማ ከንቲባ

1.2. አቅጣጫ

ሄግ በኔዘርላንድ ምዕራባዊ የባህር ጠረፍ በደቡባዊ ምእራብ ሆላንድ ግዛት ውስጥ የምትገኝ ከተማ ነች፡፡ ስያሜዋም በደች ቋንቋ ዴን ሃግ በመባል ትታወቃለች፡፡ ከተማዋ ከአምስተርዳም ደቡብ ምዕራብ 60 ኪ.ሜ ርቀት ላይ እና ከሮተርዳም በስተሰሜን 20 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ትገኛለች፡፡ ሄግ በ 52.0705° N ኬክሮስ እና 4.3007° E ኬንትሮስ ትገኛለች፡፡ (Wikipedia, 2023).



ፎቶ 3፡- ሄግ ከተማ ከደቡብ ኔዘርላንድ ያለው አቅጣጫ

1.3. ኢኮኖሚ

የከተማዋ የሀገር ውስጥ ምርት (GDP) ይበልጥ እንዲጠናከር ካደረጉት ምክንያቶች መካከል እንደ አለም አቀፉ የፍትህ ፍርድ ቤት እና አለም አቀፉ የወንጀለኞች ፍርድ ቤት ያሉ በርካታ አለምአቀፍ ተቋማትን በማስተናገድ አለም አቀፍ ማዕከል በመሆኗ ነው። ሄግ ከተማ የተረጋጋ እና ለኢኮኖሚያዊ ቀውሶች የማይበገር ኢኮኖሚ ገንቢታለች። እ.ኤ.አ በ2022 ሄግ ከተማ 4.5 በመቶ የኢኮኖሚ ዕድገት አስመዝግባለች። እንደ የዋጋ ንረት እና ጂኦፖለቲካል አለመረጋጋት ያሉ ተግዳሮቶች ቢኖሩም የከተማዋ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ የተረጋጋ ነው። (ELIRES, 2023)

1.3.1. የከተማዋ ቁልፍ የኢኮኖሚ ዘርፎች መካከል በከፊል

ሀ/ አለም አቀፍ ድርጅቶች እና ለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶች (International Organizations and Non Profits):- ሄግ የአለም አቀፉ ፍርድ ቤትን ጨምሮ በቋጥር ከ200 በላይ አለም አቀፍ ድርጅቶች ይገኛሉ። የነዚህ ድርጅቶች በከተማው መገኘታቸው ለ40,000 ሰዎች የስራ እድል ፈጥረዋል። ይህም በሄግ ከተፈጠሩ ጥቅል የስራ እድሎች ውስጥ ¼ በመቶው የሚሆነው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከእነዚህ ድርጅቶች ጋር የተገናኘ ነው። (Municipality of The Hague, 2023)

ለ/ የኮርፖሬት ዋና መሥሪያ ቤት (Corporate Headquarters):- ከተማዋ እንደ አጎን፣ ኤንቢሲ ባንክ እና ሲመንስ (Aegon, NIBC Bank, and Siemens) እና ሌሎችም ያሉ ግዙፍ የሆኑ የበርካታ ዓለም አቀፍ ኩባንያዎች መቀመጫ ናት። እነዚህ ተቋማት ለሄግ ከተማ የፋይናንስ፣ የቴክኖሎጂ እና የሎጂስቲክስ ማዕከልነት መሆን አስተዋፅኦ አድርገዋል። (The Hague International Centre, 2023)

ሐ/ የህግ እና የፋይናንስ አገልግሎቶች (Legal and Financial Services):- በሄግ ከተማ እንደ የመንግስት መቀመጫነቷ የህግ የንግድ ድርጅቶችን እና የህግ ምሁራንን ያካተቱ በርካታ የህግ ሴክተር ድርጅቶች አሉ። ይህ ሴክተር ለሄግ የሚያበረክተው ኢኮኖሚያዊ አስተዋጽዎ ከተማዋ በህግ እና በሰብአዊ መብቶች ላይ ባላት አለም አቀፍ ትኩረት ነው። (The Hague International Centre, 2023)

ሙ/ ቱሪዝም (Tourism)፡- ቱሪዝም ሌላው ለሄግ ጠቃሚ የኢኮኖሚ ዘርፍ ነው። እ.ኤ.አ በ2012 ከተማዋ 1.2 ሚሊዮን ቱሪስቶችን ተቀብላ በማስተናገድ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም አግኝታለች። ቱሪስቶች በአማካኝ €2 ቢሊዮን ሄግ ከተማ ላይ ያጠፋሉ። (Wikipedia, 2023)

1.3.2. የሥራ እድል ፈጠራ

የከተማዋ የስራ አጥነት መጠን 11.5 በመቶ ሲሆን ከኔዘርላንድ አገራዊ የስራ አጥነት ደረጃ ጋር ሲነፃፀር ከሶስት እጥፍ በላይ ይበልጣል (አገራዊ የስራ አጥነት ደረጃ 3.4 በመቶ ነው)። (CBS, 2023) የስራ አጥነት መጠን በክፍለከተሞች መካከል ይለያያል። ለምሳሌ በቬስትንሃን ከፍለከተማ የስራ አጥነት መጠን 6.6 በመቶ ሲሆን እንደ ላክ እና አስካምፑ ባሉ ከፍለከተሞች ደግሞ ወደ 15.2 በመቶ እና 14.6 በመቶ በቅደም ተከተል ነው።

የስራ አጥነት ችግሮችን ለመቅረፍ ከተማ አስተዳደሩ በርካታ የከተማ ልማት ፕሮጀክቶችን ተግባራዊ እያደረገ ይገኛል። በአንዣሩ እንደ ቬስትንሃን ያሉ የበለፀጉ ክፍለከተሞች በጣም ዝቅተኛ የስራ አጥነት መጠን 6.6% አላቸው። (Gemeente Den Haag, 2023) በሄግ ያለው የስራ አጥነት ሁኔታ በዋናነት ከፍተኛ የስደት ታሪክ ያላቸው ነዋሪዎችን ያካትታል። (CBS, 2023) ወደ ከተማዋ በስደት የመጡ ነዋሪዎች ቁጥራቸው ከፍተኛ ሲሆን ከአጠቃላይ ከህዝቡ ውስጥ 45.3% ብቻ የኔዘርላንድ ተወላጆች ናቸው። (Gemeente Den Haag, 2023)



ፎቶ 4፡- የሄግ ከተማ የስራ አጥነት መረጃ በመቶኛ

1.4. የሄግ ከተማ መስህቦች በከፊል

ሀ/ ማዱሮዳም (Madurodam)፡- ማዱሮዳም እኤአ ሐምሌ 2 ቀን 1952 የተመሰረተ ሲሆን መታሰቢያነቱም በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት ለአገሩ ነጻነት ሲታገል ለነበረው ጆርጅ ማዱሮ ማስታወሻነት ነው። በሄግ ቬቨኒንገን ከፍለ-ከተማ ውስጥ የሚገኝ ሲሆን ከከተማው መሃል እና ከባህር ዳርቻው በቀላሉ ተደራሽ ነው። የማዱሮዳም ፓርክ ዋነኛ ዓላማ የኔዘርላንድን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ የቴክኖሎጂ እድገትን እና ልምላሜን በሚገልጽ መልኩ በእነስተኛ ስፍራ ለጎብኝዎች ማስተዋወቅ ነው።

ማዱሮዳም ታዋቂ የኔዘርላንድ ትልልቅ ምእራፎችና ምልክቶች፣ ታሪካዊ ከተሞች እና የልማት ስራዎችን 1:25 ስኬል መጠን ባለው ሞዴሎች የተሞላ መናፈሻ ፓርክ (Miniature Park) እና የቱሪስት መስህብ ነው። ፓርኩ በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች የተከፈለ ነው። እነሱም በኔዘርላንድ ፈጠራዎች እና ዲዛይን የሚያተኩር ስፍራ፣ በውሃ ጉዳይ እና በኔዘርላንድ መካከል ያለውን ግንኙነት ጎላ አድርጎ የሚያሳይ ስፍራ እንዲሁም የታሪካዊ የከተማ ማዕከላት ማሳያዎችን ያሳያል። (Netherlands Tourism, 2023)

ከዚህ በተጨማሪም የሊጆች መመጫወቻ ሜዳዎች እና የመመገቢያ ስፍራዎችን አካቷል። እንዲሁም ጎብኚዎች የማስታወሻ ፅታዎችን የሚገዙባቸው ሱቆችም ይገኛሉ። (Madurodam, 2023) ፓርኩ ማዱሮዳም ፋውንዴሽን በመባል በሚታወቅ ለትርፍ ያልተቋቋመ የግል ፋውንዴሽን ባለቤትነት የተያዘ ሲሆን የሄግ ከተማ ማዘጋጃቤት ከቱሪዝም ገቢ፣ ከስራ እድል ፈጠራ፣ ባህልና ታሪክን በማስተዋወቅ እና ህዝባዊ ኩነቶችን በማስተናገድ ከሚገኙ ልዩ ልዩ ገቢዎች ተጠቃሚ ነው። ቦታውን በተንቀሳቃሽ ምስል ለመመልከት የሚከተለውን የዩቲዩብ ሊንክ ይክፈቱ። https://www.youtube.com/watch?v=2SQ05UcN9do



ፎቶ 5፡- በሄግ የሚገኘው የማዱሮዳም ፓርክ ከፊል እይታ

ለ/ ሼቨኒንገን የባህር ዳርቻ (Scheveningen beach)፡- በሄግ የሚገኘው የሼቨኒንገን የባህር ዳርቻ በኔዘርላንድ ውስጥ ታዋቂ የባህር ዳርቻ ሪዞርት ሲሆን በየዓመቱ በሚሊዮን በሚቆጠሩ ጎብኚዎች ይጎበኛል። መዝናኛ ስፍራው ስፋት ባለው አሸዋማ የባህር ዳርቻ እና ተስማሚ የአየር ጠባይ ይታወቃል። ለጎብኝዎች እንደየእድሜያቸው ደረጃ ልዩ ልዩ የመዝናኛ አገልግሎቶችን አካቷል። ጎብኚዎች በተለይም በፀሀያማ ወራት በመታጠብ፣ በመዋኘት እና የተለያዩ የውሃ ስፖርቶችን በማከናወን ሲዝናኑ ይታያል። በባህር ዳርቻው አቅራቢያ ጎብኝዎች ትኩስ የባህር አሳ ምግቦችን የሚመገቡበት በርካታ ሬስቶራንቶች ይገኛሉ።



ፎቶ 6፡- የሼቨኒንገን የባህር ዳርቻ መስህብ ገጽታዎች

አይኮኒክ ፓይር ("iconic Pier") በባህር ዳርቻው ለተሻለ እይታ እና ለመዝናኛነት ከፍ ብሎ የተገነባ ቁስ ነው። በኮንክሪት፣ በጠንካራ ብረት እና በመሲታወት የተሰራው 382 ሜትር ቁመት ያለው የ"iconic Pier" መስህብ የባህር ዳርቻውን ማራኪነት የበለጠ በማሳደግ ለቱሪስቶች ምቹ መዳረሻ አድርጎታል።

ከመዘናኛ አቅርቦቶቹ በተጨማሪ ሼቨኒንገን የባህር ዳርቻ በየዓመቱ የተለያዩ ዝግጅቶችን በዋናነት የባህል ፌስቲቫሎችን እና የባህር ዳርቻ ፓርቲዎችን ያስተናግዳል።



ፎቶ 7፡- የሼቨኒንገን የባህር ዳርቻ በከፊል

የሼቨኒንገን የባህር ዳርቻ እና ተያያዥ መስህቦችን ባለቤትነት በተመለከተ የባህር ዳርቻው የህዝብ ሲሆን አይኮኒክ ፓይሩ ("iconic Pier") በኮንዶር ቬለልስ እና ኢጋር ድርጅቶቹ ባለቤትነት የሚተዳደር ነው። (RE:BORN Real Estate, 2024) የሼቨኒንገን የባህር ዳርቻ ለህዝብ ክፍት ሲሆን የሚተዳደረውም በማዘጋጃቤቱ ነው። ከተማው ከንብኝዎች መግቢያ ክፍያ፣ ከቱሪስት ታክስ እና ከተለያዩ ዝግጅቶች የሚገኙ ገቢዎች ተጠቃሚ ነው። ቦታውን በተንቀሳቃሽ ምስል ለመመልከት የሚከተለውን የዩቲዩብ ሊንክ ይክፈቱ። https://www.youtube.com/watch?v=fB4tf2idAgg



ፎቶ 8፡- በሼቨኒንገን የሚገኘው መዝናኛ (iconic Pier)



ፎቶ 9፡- የልምድ ለውውጡ ተሳታፊዎች በቪንትጎን የባህር ዳርቻ

ሐ/ ቢንነሆፍ (Binnenhof)፡- በሄግ መሃል ከተማ የሚገኝ ታሪካዊ የኔዘርላንድ የፖለቲካ ማዕከል ህንጻ ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት ቢንነሆፍ ሌኔቱን እና የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤትን ጨምሮ የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤትና የተለያዩ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችንም ይዟል፡፡



ፎቶ ፲፡- የኔዘርላንድ ፓርላማ (ቢንነሆፍ)

መ/ ሄት ፕሌይን እና ግሮት ማርክ (Het Plein and Grote Markt)፡- ታሞቂ የሆኑ ካፌዎች እና ሬስቶራንቶች መኖሪ ስፍራ ነው።



ፎቶ ፲፩፡- ሄት ፕሌይን እና ግሮት ማርክ

ሄት ፕሊን እና ግሮት ማርክ በሄግ ውስጥ የሚገኙ ሁለት ታሞቂ አደባባዮች ሲሆኑ ለአካባቢው ልዩ ድባብን በመፍጠር ይታወቃሉ። ግሮት ማርክ የቀድሞ የገበያ አደባባይ ሲሆን በአሁን ወቅት አካባቢው ከገበያነት ወደ መገናኛ ስፍራነት ተቀይሯል። ስፍራው በሬስቶራንቶች እና በልዩ ልዩ መገልገያዎች የተሞላ ነው።

ሠ/ የሞሪትሹይስ ሙዚየም (Mauritshuis Museum)፡- ሞሪትሹይስ በሄግ የሚገኝ በኔዘርላንድ ወርቃማ ዘመን እንደ ቬርሜር እና ሬምብራንት የመሳሰሉ ታሞቂ የጥበብ ሰዎች የሳቧቸው ሥዕሎች ለእይታ የቀረቡበት የጥበብ ሙዚየም ነው።





ፎቶ 12፡- የሞሪትሹይስ ሙዚየም

ረ/ የሰላም ቤተ-መንግስት (Peace Palace)፡- የአለም አቀፍ የፍትህ ፍርድ ቤት መቀመጫ እና የአለም አቀፍ ሰላም ምልክት ሲሆን ስራ የጀመረውም ኢ.ኤ በነሃሴ 28/ 1913 ነበር። ቤተመንግስቱም በስኮትላንዳዊ አሜሪካዊ በጎ አድራጊ አንድሪው ካርኔጊ ሶጎንቢታው የ.5 ሚሊዮን ዶላር የገንዘብ ድጋፍ የተሰራ ነው። (Wikipedia, 2023)



ፎቶ ፲፭፡- የሰላም ቤተ መንግስት መረጃ

የሰላም ቤተ መንግሥት የበርካታ ታዋቂ ዓለም ዓቀፍ ተቋማት መቀመጫ ነው። (Wikipedia, 2023) ከእነዚህም መካከል፡-

•ዓለም አቀፍ የፍትህ ፍርድ ቤት (International Court of Justice (ICJ))፡-
ይህ የተባበሩት መንግስታት ዋና የዳኝነት አካል ነው።

•ቋሚ የግልግል ፍርድ ቤት (Permanent Court of Arbitration)፡-
አለም አቀፍ አለመግባባቶችን ለመፍታት የተቋቋመ ነው።

•ሄግ የአለም አቀፍ የህግ አካዳሚ (Hague Academy of International Law)፡-
በአለም አቀፍ ህግ ዙሪያ የላቀ ትምህርት የሚሰጥ ተቋም ነው።

•የሰላም ቤተ-መጽሐፍት (Peace Palace Library)፡-
በዓለም አቀፍ ሕግ ላይ የሚያተኩር ልዩ ቤተ መጻሕፍት ነው።



ፎቶ 14፡- የሰላም ቤተ-መንግስት ተቋማት

የሰላም ቤተ መንግስት በአለም አቀፍ ደረጃ የሰላም እና የፍትህ ምልክት ሆኖ እየተለለ ይገኛል። ተቋሙ ግጭቶችን ከጦርነት ይልቅ በሀገር መንገድ የመፍታት ሀሳቦችን ያቀፈ ነው።



ፎቶ 15፡- የሰላም ቤተ መንግስት

1.5. የሄማ ከተማ አስተዳደር ህንጻ እና ሎጎ

የሄማ ከተማ አስተዳደር ህንፃ የሌይዌግ (Leyweg City Office) ከተማ ፅህፈት ቤት በመባልም ይታወቃል። ህንጻው በሄማ ኢስካምፕ (Escamp) ክፍለከተማ የሚገኝ ሲሆን ያረፈበት ቦታ ስፋት 32,600 ሜ2 ነው። የከተማ አስተዳደሩ የህንጻ ወለል (Groud Floor) የሚከተሉትን የህዝብ አገልግሎቶች እና መልዕክቶችን በማካተት የተደራጀ ሲሆን ተገልጋዮች የወረፋ ቁጥር (Public Service counters) በመያዝ አገልግሎት የሚያገኙበት ስርዓት ተዘርግቷል።

- የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎቶች የስራ ክፍሎች፡- እነዚህ የስራ ክፍሎች የፓስፖርት አገልግሎትን ጨምሮ ለነዋሪዎች በቀጥታ የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎቶችን ይሰጣሉ። ነዋሪዎች አዲስ የኔዘርላንድ ፓስፖርት፣ የነዋሪነት መታወቂያ እና የመንጃ ፈቃድ እንዲሰጣቸው ማመልከቻ የሚያቀርቡበትና የሚወስዱበት የስራ ክፍል ተደራጅቷል።
- ነዋሪዎች እነዚህን ዶክመንቶች እንዲሰጣቸው ለማመልከት ቀጠሮ የሚያስፈልግ ሲሆን ለመውሰድ ግን ቀጠሮ ሳያስፈልግ የከፈሉበትን ደረሰኝ እና መታወቂያ በመያዝ መውሰድ ይችላሉ።
- የመረጃ መልዕክት ቁሳቁሶች እና የህዝብ ቤተመፃህፍት ይዟል።

የህንጻው የመጀመሪያው ፎቅ የሰርግ አዳራሽ (wedding hall) የሰራተኞች ምግብ ቤት (staff restaurant) እና የመሰብሰቢያ አዳራሾችን ይዟል። ከ2ኛ ፎቅ በላይ ያሉ ወለሎች በከተማ አስተዳደሩ ስር የሚገኙ የተለያዩ ሴክተር መስሪያ ቤቶች ናቸው።



ፎቶ 16፡- የሄማ ከተማ አስተዳደር ህንጻ

የሄግ ሎጎ ከተማዋ የኔዘርላንድ የፖለቲካ እና የአስተዳደር ማእከል መሆኗን ያንፀባርቃል። ከተማዋ ለሰላምና ለፍትህ ያላትን ቁርጠኝነት በማሳየት የአለም አቀፍ ህግ እና የዲፕሎማሲ ማዕከል በመሆን ሚናዋን የሚያሳዩ ጉዳዮችን አካቷል።

ሎጎው የከተማዋን ልዩ መገለጫ (brand identity) በማንፀባረቅ በአገር አቀፍም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ በቀላሉ እንድትታወቅ አድርጓታል። ሎጎው የሄግ ዋና አሴቶችን ማለትም አካታችነት፣ ብዝሃት እና ለአለም አቀፍ ትብብር ቁርጠኝነትን ገላጭ በሆነ ሁኔታ ተዘጋጅቷል። ዓለም አቀፍ የፍትህ ፍርድ ቤት እና የተለያዩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ጨምሮ በርካታ ዓለም አቀፍ ድርጅቶችን የምታስተናግድ ከተማ እንደመሆኗ አርማው ለእነዚህ አሴቶች ትኩረት ሰጥቷል።



Den Haag

ፎቶ ፲፫፡- የሄግ ከተማ ሎጎ

1.6. የመንግስት መቀመጫ (Seat of Government)

ሄግ ከተማ የኔዘርላንድ መንግስት፣ የፓርላማ እና የንጉሣዊ ቤተሰብ መቀመጫ በመሆን እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ከ1588 ጀምሮ በማገልገል ላይ ትገኛለች። ሄግ የጠቅላይ ፍርድ ቤት እና የበርካታ የመንግስት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች መቀመጫ ናት። አምስተርዳም በአገሪቱ ህገመንግስት እንደተገለጸው የኔዘርላንድስ ዋና ከተማ ናት። ነገር ግን ሄግ ከተማ በተለምዶ የሀገሪቱ "ዋና ከተማ" ("de facto capital") እየተባለ ይጠራል። ሄግ ከተማ ንጉሱ የሚኖሩበት እና የሚሰሩበት እንዲሁም ብዙ የውጭ ኤምባሲዎች የሚገኙባት የኔዘርላንድ የአስተዳደር ማዕከል ናት።



ፎቶ 18፡- የሄግ ከተማ በከፊል

1.7. የመናገሻ ከተማ (Royal City)

ሄግ በታሪክ ለረዥም ጊዜ የኔዘርላንድ ነገስታት እና የመንግስት መቀመጫ በመሆኗ የኔዘርላንድ "የመናገሻ ከተማ" በመባል ትታወቃለች። ሄግ የኔዘርላንድ ንጉሣዊ ቤተሰብ መኖሪያ ሆና በማገልገል ከአራት መቶ ዓመታት በላይ የኔዘርላንድ የፖለቲካ እና የአስተዳደር ማዕከል ሆና ቆይታለች። ኔዘርላንድ በሕገ መንግሥታቸው ንጉሣዊ አገዛዝ (constitutional monarchy) አውቅና የተሰጠው ሲሆን ንጉሥ ዊለም-አሌክሳንደር የወቅቱ ርዕሰ መስተዳድር (head of state) ናቸው።





ፎቶ 19፡- የኔዘርላንድ ንጉስ እና ንግስት

1.8. ብዝሀነትን የምታስተናግድ ከተማ (Diverse City)

በከተማዋ የተለያዩ ማንነት ያላቸው የኔዘርላንድ ዜጎች፣ የተለያዩ አገራት ዜጎች ስደተኞችን ጨምሮ በመከባበር የሚኖሩባት ከተማ ነች። ሄግ በሰሜናዊ ምዕራብ ከፍተኛ ገቢ ያላቸው ዜጎች የሚኖሩባት እንዲሁም በደቡብ ምስራቅ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች የሚኖሩባት በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መለያየት (socioeconomic segregation) የምትታወቅ ከተማ ናት። የሄግ ከተማ ከጠቅላላው ነዋሪ ውስጥ ከ50% በላይ የሚሆነው ህዝብ የስደት ታሪክ (migration background) ያለው ሲሆን ይህም ከተማዋ ብዝሃትን ለማስተናገዷ አይነተኛ ምሳሌ ነው። ከዚህ በታች የሄግ ከተማ ብዝሃነት መረጃን መመልከት ይቻላል።



ፎቶ 20፡- የሄግ ከተማ ብዝሃነት መረጃ

1.9. ሜትሮፖሊታን ከተማ (Metropolitan City)

እ.ኤ.አ. ከ 2015 ጀምሮ ሄግ እና ሌሎች 20 ከተሞች በ1,200 ስኩዌር ኪሎ ሜትር ስፋት ላይ በጥቅሉ 2.4 ሚሊዮን ነዋሪዎች የሚኖሩበት የሮተርዳም-ዘ ሄግ ሜትሮፖሊታን አካባቢን መስርተዋል። አካባቢው ራንድስታድ ተብሎ የሚጠራው ትልቅ የከተማ አካባቢ አካል ነው። ይህ አምስተርዳም እና ዩትሬክትን የሚያጠቃልለው ሰሜኒ የአገሪቱ የፖለቲካል ኢኮኖሚ ማእከል ነው።

ሄግ 2 ትልልቅ የባቡር ጣቢያዎች እና 2 አለምአቀፍ አውሮፕላን ማረፊያዎች አሏት። አውሮፕላን ማረፊያዎቹም ሮተርዳም-ዘ ሄግ አለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ እና አምስተርዳም ስኪፖል አለምአቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ በመባል ይታወቃሉ። ከሄግ ማእከላዊ የባቡር ጣቢያ በመነሳት ወደ ሁለቱም አውሮፕላን ማረፊያዎች በባቡር ተጓጉዞ ለመድረስ 40 ደቂቃ ይፈጃል።

ሄግ ከሌሎች የኔዘርላንድ እና የአውሮፓ አገራት ጋር በመሰረተ ልማት የተሳሰረች ሲሆን በከተማው የተሳለጠ የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት እየተሰጠ ይኛል። ከሌሎች የአገሪቱ ዋና ዋና ከተሞች እንደ አምስተርዳም፣ ብራስልስ እና ፓሪስ ጋር ቀጥታ በፈጣን ባቡር ትገናኛለች።



ፎቶ 21፡- የሄግ ከተማ በከፊል

1.10. ሄግ በተማሪዎች ተመራጭ ከተማ (Student City)

ሄግ የላይደን ዩኒቨርሲቲ (Leiden University) እና የሄግ አፕላይድ ሳይንስ ዩኒቨርሲቲን ጨምሮ የበርካታ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት መኖሪ ስትሆን ይህም ለተማሪዎች ማራኪ መዳረሻ ያደርጋታል። ከተማዋ የዩንቨርሲቲዎች ማዕከልም (university hub) በመባል ትታወቃለች።



ፎቶ 22፡- በሄግ የሚገኘው የላይደን ዩንቨርሲቲ

1.11. አዶ ዴንሃግ ስቱዲየም

ስታዲየሙ እ.ኤ.አ በ2007 ስራ የጀመረ ሲሆን ወደ 15,000 የሚጠጉ ተመልካቾችን የመያዝ አቅም አለው። በአውሮፓ ካሉት ስታዲየሞች አንዱና ደህንቱ የተጠበቀ እንደሆነ የሚነገርለት ስቱዲየሙ በሁሉም ማዕዘኖች ላይ የስለላ ካሜራዎች እና ሲሲቲቪዎች (surveillance cameras and CCTVs) ተገጥመውለታል። ስታዲየሙ ከእግርኳስ በተጨማሪ አልፎ አልፎ ለኮንሰርቶች እና ለሌሎች የሀገር ውስጥ ዝግጅቶችም ያገለግላል። ስታዲየሙ በተለያዩ የትራንስፖርት አማራጮች በቀላሉ ተደራሽ ነው።



ፎቶ 23፡- ADO Den Haag ስታዲየም

1.12. ሄግ የቱሪስት መዳረሻ ከተማ (Tourist Friendly City)

ከኔዘርላንድ ከተሞች መካከል ሄግ ከተማ ከአምስተርዳም በመቀጠል 2ኛዋ የቱሪስት መዳረሻ ከተማ ናት። በከተማዋ ከ30 በላይ ሙዚየሞች፣ ፓርኮች እና የባህል ማእከላት ይገኛሉ።



ፎቶ 24፡- የሄግ ከተማ የቱሪስቶች መዳረሻ በከፊል

1.13. ሄግ የሰላም እና የፍትህ ማዕከል (The Hague as a Hub for Peace and Justice)

ሄግ የአለም አቀፍ ህግ እና የግልግል ዳኝነት ማዕከል (international law and arbitration)፣ አለም አቀፍ የፍትህ ፍርድ ቤት (International Court of Justice) ፣ አለም አቀፍ የወንጀለኞች ፍርድ ቤት (International Criminal Court) እና ሌሎች ከ480 በላይ አለም አቀፍ ድርጅቶችን የሚያስተናግድበት ዓለም አቀፍ ማዕከል በመባል ይታወቃል።

1.14. የመንግስታት ትብብር እና ያልተማከለ አስተዳደር (Intergovernmental Cooperation and Decentralization)

1.14.1/ በሄግ ከተማ የመንግስታት ትብብር

የአለም አቀፍ የሰላም እና የፍትህ ከተማ በመባል የምትታወቀው ሄግ የበርካታ አለም አቀፍ ድርጅቶችን እና ተቋማትን በማስተናገድ በመንግስታት ትብብር ውስጥ ልዩ ቦታ አላት። በዚህም ምክንያት ሄግ የኢኮኖሚ ዕድገት፣ ዓለም አቀፍ ክብር፣ የዕውቀት ልውውጥ፣ የባህል ልዩነት እና የሥራ ዕድል ፈጠራ ተጠቃሚ ሆናለች። በሄግ ያለው የመንግስታት ትብብር መገለጫ ከብዙ በጥቂቱ የሚከተሉትን ይመሰላል፡-

ሀ/ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች

ከተማዋ እንደ ዓለም አቀፍ የፍትህ ፍርድ ቤት (ICJ)፣ ዓለም አቀፍ የወንጀል ፍርድ ቤት (ICC)፣ የግልግል ችሎት ቋሚ ፍርድ ቤት (PCA)፣ የኬሚካል ጦር መሳሪያዎች ከልከላ ድርጅት (Organisation for the Prohibition of Chemical Weapons (OPCW))፣ ኢሮፖል(European Union Agency for Law Enforcement Cooperation) እና የሮጄስት (EU Agency for Criminal Justice Cooperation) የመሳሰሉ ተቋማት መኖሯ ናት። (Wikipedia, 2023)



ፎቶ 25፡- በሄግ ከተማ የሚገኘው አለም አቀፍ የሰብሰባ ማዕከል

ለ/ ዲፕሎማሲያዊ መገኛ

ሄግ ከ180 በላይ አለም አቀፍ ድርጅቶች፣ በርካታ ኤምባሲዎችና ቆንስላ ፅህፈት ቤቶች፣ አለም አቀፍ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና የጥናት ማህበራት (think tanks) በማስተናገዷ ለዲፕሎማሲ እና ለዓለም አቀፋዊ ትብብር ማዕከል አድርጓታል። (The Hague International Centre, 2023)

ሐ/ ተቋማዊ ማዕቀፍ

የሄግ ከተማ አስተዳደር ከአገሪቱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመቀናጀት እና የደህንነት የትብብር ማዕቀፎችን መሰረት በማድረግ የእነዚህን ዓለም አቀፍ ተቋማት ስራቸውን በአግባቡ እንዲያከናውኑ እየደገፈ ይገኛል። (CILC፣ 2023)

መ/ የትብብር ዘዴዎች

- የደህንነት ቅንጅት፡- ይህ የጋራ የደህንነት ፕሮቶኮሎችን፣ የአደጋ ጊዜ ምላሽ አቅድን፣ የመረጃ ልውውጥን እና የዲፕሎማቲክ ጥቢቃ አገልግሎቶችን ያካትታል።
- አስተዳደራዊ ድጋፍ፡- ለአለም አቀፍ ድርጅቶች የአንድ ማዕከል አገልግሎት በመስጠት ስራተኞች የመኖሪያ ቤት ድጋፍን፣ ምዝገባ እና ፍቃድ ማመቻቸትን ያካትታል።

• ኢኮኖሚያዊ ትብብር፡- በሄግ በአውቶት መጋራት መድረኮች፣የፈጠራ ማዕከሎች እና የምርምር ተቋማት አማካኝነት ዓለም አቀፍ የንግድ ትርኢቶችን በማዘጋጀት የእርስ በርስ ትብብር እንዲኖሰብት እየተሰራ ይገኛል፡፡ (The Hague University of Applied Sciences, 2023).

ሠ/ ቁልፍ የትብብር መስኮች

• በሀግ እና ፍትህ ዘርፍ በአለም አቀፍ ሀግ ልማት፣ በዳኝነት ትብብር፣ በሀግ አውቶት ልውውጥ እና በአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች ላይ ትኩረት ተደርጓል፡፡

• ከሰላምና ደኅንነት አንፃር ግጭቶችን መፍታት፣ የሰላም ማስከበር ጥረቶች፣ የጸጥታ ፖሊሲ ልማት እና የቀውስ አስተዳደርን ያካትታሉ።(OECD iLibrary, 2023)

1.14.2/ ያልተማከለ አስተዳደር

ሄግ ከተማ ባልተማከለ አስተዳደር መርህ መሠረት በፖለቲካ፣ በአስተዳደርና በሃብት ከፍፍል ተገቢው ነጻነት በአገሪቱ ሀግ የተሰጠው ሲሆን በማስፈጸም አቅም ተጠናክረው የህዝቡን የልማትና የአገልግሎት ፍላጎት በማርካት ብዙ ርቀት ተጉዘዋል፡፡ የሄግ ከተማ ነዋሪዎች የስልጣን ባለቤት የሆኑበት ፖለቲካዊ ስልጣን በአገሪቱ ህገመንግስት የተረጋገጠ ነው፡፡ ከተማዋ ከማእከላዊ መንግስት ጋር ያላትን ግንኙነት በማጠናከር ራስን በራስ በማስተዳደር የምትታወቅ ከተማ ናት፡፡

ሀ/ የአስተዳደር መዋቅር

የከተማው ምክር ቤት (Gemeenteraad) በህዝብ የተመረጡ ተወካዮችን በአባልነት ያቀፈ ሲሆን ምክርቤቱም የከተማው ከፍተኛ የአስተዳደር ስልጣን ባለቤት ነው፡፡ የምክርቤቱ አባላት የፖሊሲ ማውጣት፣ በጀት የማጽደቅ እና ስትራቴጂክ አቅድ የማዘጋጀት ሃላፊነት ተሰጧቸዋል፡፡ (The Hague Municipal Council, 2023) ሄግ ከተማ የከተሞች የእርስ በርስ ግንኙነት እና አለማቀፍ ልምድ የምትቀስምበት ዘዴ የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡፡

• ሄግ እና በዙሪያዋ ያሉ ከተሞችን ያቀፈው የሀግላንደን ክልላዊ ባለስልጣን መ/ቤት (Haaglanden region) የትራንስፖርት፣ የኢኮኖሚ ልማት እና የአካባቢ ጥበቃ ፖሊሲዎችን ያስተባብራል፡፡

• ዘሄግ ከተማ የኔዘርላንድ ከተሞች ማህበር (VNG) አባል በመሆኗ ማህበሩን በመጠቀም ከሌሎች ከተሞች ጋር በተለያዩ ርእሰ ጉዳዮች ላይ ልምድ ትለዋወጣለች፡፡

• ዘሄግ ከተማ የአለም አቀፍ ከተማ/ካውንቲ ማኔጅመንት ማህበር (International City/County Management Association (ICMA)) አባል በመሆኗ በከተማ አስተዳደር ላይ የእውቀት እና የተሞክሮ ልምድ ልውውጥ ታደርጋለች።
የከተማዋ ራስን በራስ የማስተዳደር እና የብዝሃ-ደረጃ ቅንጅት ጥምረት ዘሄግ ከተማ የአለም አቀፍ አስተዳደር ማዕከል ሚናዋ እንዲቀጥል አስችሏታል። ለከተው ነዋሪዎች የአገልግሎት እና ጥያቄዎች ፋጣን ምላሽ ለመስጠት ምቹ ሁኔታን ፈጥሮላታል።

ከተማዋ በአገልግሎት አሰጣጥ፣ በህብረተሰብ ተሳትፎ እና በከፍለከተማ-ተኮር እቅድ ላይ በሚያተኩሩ ስምንት የአስተዳደር ከፍለከተሞች (Stadsdelen) የተከፋፈለ ነው። ከፍለከተሞቹም ሴንትረም፣ ኢስካምፐ፣ ሃግስ ሀውት፣ ላክ፣ ላይደሸንዚ-ዮፔንበርግ፣ ሎሰዳይንን፣ ሼቨኒንገን እና ሴግበርከ በመባል ይታወቃሉ። እነዚህ የከፍለከተማ ምክር ቤቶች እንደ የሰፈር ልማት፣ የማህበረሰብ አገልግሎቶች እና ከፍት የህዝብ ቦታዎች ለመሳሰሉ አካባቢያዊ ጉዳዮች ላይ የመወሰን ስልጣን አላቸው። (Wikipedia, 2023)

ለ/ ያልተማከለ አገልግሎቶች (Decentralized Services)

የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎቶች የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ፣ የህዝብ ከፍት ቦታ አገልግሎት፣ የህዝብ ትራንስፖርት ድጋፍ፣ የትምህርት አገልግሎቶች የሰነድ ማረጋገጫ፣ የምዘገባ አገልግሎት፣ የመረጃ አቅርቦትን እና የማህበራዊ ደህንነት ፕሮግሞችን ያጠቃልላል። የማህበራዊ አገልግሎቶች በማህበረሰብ ማእከላት አማካኝነት የማህበረሰብን ደህንነት ለማሻሻል የወጣቶች አገልግሎት፣ የአረጋውያን እንክብካቤ እና ማህበራዊ ድጋፍ ይሰጣሉ።

የሕዝብ ከፍት ቦታ አስተዳደር ሃላፊነቶች የፓርክ ጥገና፣ የመንገድ ጽዳት፣ የመሠረተ ልማት አስተዳደር እና የከተማ ፕላን ስራዎችን ያካትታል። ከተማዋ የነዋሪውን ፍላጎቶችን ለመመለስ የስፖርት ማዕከላትን፣ ቤተመጻሕፍትን፣ የባህል ማዕከሎችን እና የጤና አጠባበቅ አገልግሎቶች እየተሰጡ ይኖራል። (The Hague Municipal Organisation, 2023)

ሐ/ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት

በከፍለከተማ ደረጃ የወሳኔ አሰጣጥ ሂደቱ የከፍለከተማው ልዩ ልዩ ኮሚቴዎችን (ምሳሌ አማካሪ ኮሚቴ) የሚያሳትፍ ሲሆን ይህም የነዋሪዎችን ተሳትፎ በእጅጉ ያበረታታል። በከተማ ደረጃ የፖሊሲ ቅንጅት እና የሀብት ድልድል በከተማ ደረጃ የሚከናወን ስራ ሲሆን ይህም ስትራቴጅካዊ አካሄድ ለመከተል እና በከፍለከተሞች መካከል ያለውን ትብብር ለማጎልበት ረድቷል። (The Hague Municipal Organisation, 2023)

መ/ የህብረተሰብ ተሳትፎ

የህብረተሰብ ተሳትፎ በክፍለከተማ ምክር ቤቶች፣ በህዝባዊ ስብሰባዎች፣ እና በኦንላይን መድረኮች መደበኛ ቻናሎች ይገለጻል። መደበኛ ያልሆኑ ቻናሎች በዋናነት የሰፈር ሚህበራት እና የማህበረሰብ ስብሰባዎች የዲጂታል ተሳትፎን እና የማህበራዊ ሚዲያ ተሳትፎን በማበረታታት ይታወቃሉ። (The Hague Municipal Council, 2023)

ሠ. የፋይናንስ አስተዳደር

ለክፍለከተሞች በጀት የሚመደው በክፍለከተማው ቅድሚያ በሚሰጣቸው ጉዳዮች፣ በፕሮጀክት-ተኮር የፓዝብ ድጋፍ እና በአፈጻጸም ክትትል ላይ በመመስረት ነው። በፍላጎት ላይ የተመሰረተ የበጀት ድልድል የህዝብ ብዛትን፣ የአካባቢ-ተኮር ተግዳሮቶችን ታሳቢ በማድረግ እና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን የልማት ጉዳዮች ምላሽ ለመስጠት ግምት ውስጥ ያስገባል። (The Hague Municipal Organisation, 2023)

ክፍል ሁለት

የሄግ ከተማ ዘላቂ የትራንስፖርት መሠረተ ልማት እና አገልግሎት

በሄግ በኤሌክትሪክ የሚሰሩ የከተማ ውስጥ ቀላል ባቡሮችን (trams)፣ አውቶቡሶችን እና አገር አቋራጭ ባቡሮችን ያካተተ የመጓጓዣ አማራጮችን ተግባራዊ ተደርጓል። የከተማው የህዝብ ማመላለሻ ስርዓት ኤችቲኤም HTM (The Hague Tramway Company) በተባለ መንግስታዊ ተቋም የሚመራ ሲሆን በከተማው ውስጥ ሰፊ የትንስፖርት ሽፋን እንዲኖር በማስቻል እና ከከተማው ዙሪያ ካሉ አካባቢዎች ጋር ትስስር በመፍጠር ውጤታማ ስራዎችን በማከናወን ላይ ይገኛል።

ኤችቲኤም በከተማዋ ቀላል የከተማ ባቡሮችን (Trams) እና አውቶቡሶችን የሚያስተዳድር ተቋም ነው። ኤችቲኤም ለነዋሪዎች እና ጎብኝዎች ቀልጣፋ እና ምቹ የህዝበ መጓጓዣን በማመቻቸት የትራፊክ መጨናነቅን ለመቀነስ እና ዘላቂ የትራንስፖርት አማራጮችን በማስተዋወቅ ረገድ ወሳኝ ሚና ተጫውቷል።

ሁሉን አቀፍ እና ዘላቂ የትራንስፖርት ስርዓትን ለመዘርጋት እንዲረዳ ከተማው ምቹ የባቡር፣ የመኪና፣ የብስክሌት እና የእግረኛ መንገዶችን እንዲሁም የባቡር ጣቢያዎችን የሳይክል ፓርኪንጎችን፣ የአውቶብስ ፈርማታዎችን ዘርግቷል። ይህ አንቅስቃሴን ከማሳለጥ ባሻገር የካርበን ልቀትን ለመቀነስ እና ጤናማ የከተማ አካባቢን ለመፍጠር ጠቀሚታው የጎላ ነው።

2.1. በሄግ ከተማ ዋና ዋና የመጓጓዣ ዘዴዎች

2.1.1. የህዝብ ትራንስፖርት

ሀ/ የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት (Trams)

ይህ ዓይነቱ የባቡር ትራንስፖርት እ.ኤ.አ. በ 1864 የተመሰረተ ሲሆን ታሪካዊ መሰረቱን በመጠበቅ ከጊዜ ወደጊዜ ከከተማ ነዋሪዎች ፍላጎቶች ጋር በመስማማት ለአመታት በከፍተኛ ሁኔታ እየተሻሻለ መጥቷል። በሄግ የመጀመሪያዎቹ የዚህ የትራንስፖርት ዓይነት ፉርጎዎች በፈረሶች በመታገዝ የሚጉተቱ የነበሩ ሲሆን በ19ኛው ክፍለ ዘመን መገባደጃ ላይ በእንፋሎት ሀይል በሚሰሩ ባቡሮች መተካት ጀመሩ።



ፎቶ 26፡- በሄግ የመጀመሪያው በፈረስ ተጎታች ባቡር (እ.ኤ.አ ሰኔ 23, 1864)

በሄግ የመጀመሪያው የኤሌክትሪክ የከተማ ቀላል ባቡር መስመር እ.ኤ.አ. በነሀሴ 1904 አገልግሎቱን በመጀመር በእንፋሎት ሃይል የሚሰሩ የከተማ ቀላል ባቡሮችን ተክቷል። (Wikipedia, n.d.)



ፎቶ 27፡- በእንፋሎት ኃይል በሚሰሩ ባቡሮች

የሄግ የከተማ የኤሌክትሪክ ባቡር ትራንስፖርት ዓይነት ወደ 117 ኪሎ ሜትር ርዝመት ያላቸው የባቡር ሀዲዶች እና 241 ማቆሚያ ስፍራዎችን ያቀፈ ነው። በሄግ በአማካይ ከ275,000 በላይ መንገደኞች

በኤሌክትሪክ የሚሰራ የከተማ ቀላል ባቡርን በየቀኑ ይጠቀማሉ። ይህ ዓይነት የባቡር ስርዓት ተደራሽ እና ከመሬት ያላቸው ከፍታ ዝቅተኛ በመሆኑ ለሁሉም ተሳፋሪዎች በቀላሉ ለመሳፈር አመቺ ናቸው። (HTM, n.d.)

በሄግ በአሁን ወቅት በእንፋሎት ሃይል የሚሰራ የከተማ ቀላል ባቡር ባይኖርም የሕዝብ ትራንስፖርት እንዲስፋፋና ቅልጥፍና እንዲፈጠር አስተዋጽኦ አድርጓል። በአሁን ወቅት በኤሌክትሪክ የሚሰራው የከተማው ቀላል ባቡር በኤችቲኤም "Personenvervoer" በተሰኘ መንግስታዊ ተቋም የሚመራ እና የተለያዩ ዓይነት ዘመናዊ ባቡሮችን በማካተት አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል። (HTM, n.d.)

የተወሰኑ ታሪካዊ የእንፋሎት የከተማ ባቡሮች እና ተዛማጅ ቅርሶች በሙዚየሞች ውስጥ ተጠብቀው ይገኛሉ፤ ይህም በኔዘርላንድ የህዝብ ትራንስፖርት እድገት ውስጥ ያላቸውን ጠቀሜታ እንዲቶ ያሳያል። (Dutch Railway Museum, n.d.) በአሁን ወቅት በሄግ አገልግሎት ላይ በመሰጠት የሚገኘው በኤሌክትሪክ የሚሰራ የከተማ ቀላል ባቡር የከተማዋ የህዝብ ማመላለሻ ስርዓት ወሳኝ አካል ነው። ከዚህ ቀጥሎ በሄግ የኤክትሪክ ሃይል የሚሰሩ የከተማ ቀላል ባቡር ዓይነቶችን እንመለከታለን፡-

• የአቬኒዮ አይነት (Avenio type)

እ.ኤ.አ ከ2015 ጀምሮ ኤችቲኤም (HTM) በሄግ እና በአካባቢው 70 የአቬኒዮ ዓይነት (Avenio type) የከተማ ባቡሮችን ወደ ስራ አስገብቷል። አቬኒዮ ዘመናዊ የከተማ የባቡር ዓይነት ሲሆን ከፍታው ከወለል ዝቅ ያለ በመሆኑ በዊልቸር ለሚንቀሳቀሱ፣ የህጻን ማንሸራሸሪያ ጋሪ ለሚጠቀሙ እና ለህጻናትና ለአረጋዊያን የበለጠ ተደራሽ እና ምቹ ያደርገዋል። ኤችቲኤም የከተማ ቀላል ባቡር የተጠቃሚዎችን ፍላጎት መሰረት በማድረግ ዘመናዊ፣ ቀልጣፋ እና የድምጽ ብክለት የሌለው የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል። አቬኒዮ የከተማ ባቡር ዓይነቶች በነጭ/በቀይ እና በግራጫ/በቀይ ቀለሞች ተውበው ለአገልግሎት ውለዋል። ይህ የከተማ ባቡር ዓይነት ሰፋና ረዘም ያለ በመሆኑ የተሳፋሪ መጫኛ እና ማውረጃ ቦታዎች ይህንን ታሳቢ በማድረግ ተዘጋጅተዋል። (HTM, n.d.)



ፎቶ 28፡- በሄግ በኤሌክትሪክ የሚሰራ የከተማ ቀላል ባቡር (Trams)

- ሜትሮ/የራንድስታድሬይል ባቡር

ከአቪኒዮ የባቡር ዓይነት አገልግሎት በተጨማሪ ኤ.ኤ.ኤ ከ2006 ጀምሮ ኤችቲኤም (HTM) በሄግ እና በአካባቢው በርካታ የራንድስታድሬይል ዓይነት የከተማ ባቡሮችን ወደ ስራ አስጉቢቷል። ራንድስታድሬይል የባቡር ዓይነት የሄግ ከተማን ከአጎራባች ከተሞች መንገደኞችን በማጓጓዝ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል። ራንድስታድሬይል (RandstadRail) ዘመናዊ የከተማ የባቡር ዓይነት ሲሆን ከፍታው ከወለል ዝቅ ያለ በመሆኑ ለአካል ጉዳተኞች እና የህጻን ማንሸራሸሪያ ጋሪ ለሚጠቀሙ መንገደኞች የበለጠ ተደራሽ እና ምቹ ያደርገዋል። (HTM, n.d.)



ፎቶ 29፡- በሄግ በኤሌክትሪክ የሚሰራ የከተማ ቀላል ባቡር (Trams)

- ጂቲኤል (GTL tram) ቀይ-ቢኘ የከተማ ባቡር ዓይነቶች

የኤችቲኤም (HTM) ቀይ-ቢኘ የባቡር ዓይነቶች በሄግ ከተማ እና በአካባቢው ላለፉት አስርት አመታት አገልግሎት እየሰጡ ይገኛል። እነዚህ የባቡር ዓይነቶች በሁሉም የሄግ ከተማ ነዋሪዎች የሚታወቁ እና ከተማው ውበቶች ናቸው። በዚህ ጂቲኤል (GTL tram) የባቡር ዓይነት አሽከርካሪው በከፍት ካቢኔ ውስጥ ይቀመጣል። ሁሉም ባቡሮች የቲኬት መሸጫ ማሽኖች ተገጥመላቸዋል። የዚህ የባቡር ዓይነት ለአካል

ጉዳተኞች እና የህጻን ማንሸራሸሪያ ጋሪ ለሚጠቀሙ መንገደኞች ጠባብ መግቢያ ስላላቸው በቀላሉ ተደራሽ አይደሉም። (HTM, n.d.)



ፎቶ 30፡- በሄግ በኤሌክትሪክ የሚሰራ የከተማ ቀላል ባቡር (Trams)

በሄግ የባቡር ጣቢያዎች

ዴን ሀግ ሴንትራል (Den Haag Centraal) እና ዴን ሀግ ኤችኤስ (ሆላንድ ስፖር) (Den Haag HS (Hollands Spoor)) በሄግ ከተማ ከሚገኙ የባቡር ጣቢያዎች መካከል ናቸው። ሁለቱም የባቡር ጣቢዎች የበርካታ ባቡር መነሻ እና መድረሻ የሆኑ ዘመናዊ የባቡር ጣቢያዎች ናቸው።

እነዚህ የባቡር ጣቢያዎች ለተጠቃሚዎች የባቡር ሽፋንን በተራት በማረጋገጥ ከሀገር አቀፍ እና ከአውሮፓ የባቡር ኔትወርኮች ጋር የሚያገናኙ ሲሆን ተጠቃሚዎች ካሉበት የባቡር ጣቢያ ሆነው ወደ ሚፈልጉት የኔዘርላንድ ከተማ (ለምሳሌ አምስተርዳም፣ ሮተርዳም እና ኡተረክት) እና የአጎራቦች አገራት ከተሞች መሄድ ይችላሉ።

እነዚህ የመሰረተ ልማት አውታሮች እና አገልግሎቶች ሄግ ከተማን ውብ፣ ምቹ እና ዘላቂ ከተማ (sustainable city) እንድትሆን በማስቻል የግእከላዊ መንግስት እና የበርካታ አለም አቀፍ ተቋማት መቀመጫ እንድትሆን አስችሏታል። በዴን ሀግ ሴንትራል እና ዴን ሀግ ኤች ኤስ የባቡር ጣቢያዎች መካከል በሰዓት ስድስት ባቡሮች ምልልስ ያደርጋሉ። ይህም በከተማው ውስጥ ቀልጣፋ መጓጓዣ እንዲኖር አስችሏል። ይህ የአገልግሎት ድግግሞሽ ተሳፋሪዎች ምቹ የመጓጓዣ አማራጮች እንዲኖራቸው ያደርጋል።




ፎቶ 31፦ ዴን ሀግ ሲንትራል እና ዴን ሀግ ኤች ኤስ የባቡር ጣቢያዎች በከፊል

የሄግ የባቡር ትራንስፖርት ሥርዓት ከሌሎች የህዝብ ማመላለሻ ዓይነቶች ለምሳሌ የአውቶብስ እና የከተማ ቀላል ባቡር አገልግሎቶችን ጨምሮ በሚገባ የተቀናጀ ነው። ከ30 በላይ የከተማ ቀላል የባቡር መስመሮች እና ከ60 በላይ የአውቶቡስ መስመሮች የተቀናጁ ሲሆን ይህም ተጠቃሚዎች በተለያዩ የመጓጓዣ ዘዴዎች መካከል በቀላሉ እንዲሸጋገሩ ያስችላቸዋል። እንዲህ ዓይነቱ ውህደት የተለያዩ የጉዞ ፍላጎቶችን በማስተናገድ የበለጠ ቀልጣፋ እና ተለዋዋጭ የጉዞ አማራጮችን አመቻችቷል። በጣቢያዎቹ የአጠቃቀም ምልክቶች እና የጊዜ ሰሌዳ ማሳያዎች መሞራቸው ተጓዦች የባቡር መነሻ፣ መዳረሻ እና ጊዜን እንዲያውቁ አግዟቸዋል።

በሄግ የባቡር ትራንስፖርትን የበለጠ ለማሳደግ በመሰረተ ልማት ማሻሻያዎች ላይ በማተኮር እና የአገልግሎት ድግግሞሽን ለመጨመር እቅድ ተይዞ እየተሰራ ይገኛል። ይህም እየጨመረ የመጣውን ፍላጎት ለማስተናገድ እና የባቡር ሥርዓቱን አጠቃላይ ውጤታማነት ለማሻሻል ያግዛል ታምኖበታል።

በሄግ ያለው የባቡር ትራንስፖርት አጠቃቀም የትራፊክ መጨናነቅንና የካርቦን ልቀትን ለመቀነስ ይረዳል። ብዙ የከተማው ነዋሪዎች ለጉዟቸው ባቡሮችን ስለሚጠቀሙ በከተማ እንቅስቃሴ እና በካርቦን ልቀት ላይ ያለው አወንታዊ ተፅእኖ ጉልህ ነው።

ለ/ የህዝብ አውቶብስ ትራንስፖርት አገልግሎት

በሄግ በኤችቲኤም (HTM) የሚተዳደሩ እና በምሽት የሚሰሩ አውቶብሶችን ጨምሮ ከ60 በላይ የአውቶቡስ መስመሮች አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ። ኤችቲኤም በቀን እስከ 50,000 ለሚደርሱ ነዋሪዎች አገልግሎት የሚሰጡ በርካታ በተፈጥሮ ጋዝ እና በኤሌክትሪክ የሚሰሩ አውቶብሶች አሉ። አውቶቡሱ በጉዞ ወቅት ከሾፈሩ ጀርባ በሚኖኝ ስክሪን የፈርማታ መዳረሻዎችን መረጃ በምስልና በድምጽ

ይሰጣል:: የዚህ ዓይነት አውቶቡሶች ለአካል ጉዳተኞች፣ ለአረጋውያን እና ለነፍሰ ጡር ሴቶች ልዩ የተጠበቁ መቀመጫዎችን ያካተተ ነው፤ ለተሳፋሪዎችም በሚሳፈሩበት እና በሚወርዱበት ጊዜ ለመሬት ቅርብ የሆነ መወጣጫ የተገጠመላቸው ናቸው:: (HTM, n.d.; Den Haag.com, 2023)



ፎቶ 32:- በተፈጥሮ ጋዝ እና በኤሌክትሪክ ሃይል የሚሰሩ የህዝብ አውቶብሶች

የቲኬት አቆራረጥ ስርዓትን በተመለከተ ተሳፋሪዎች OV-chipkaartን ማለትም ንክኪ የሌለው ካርድ በመጠቀም የህዝብ አውቶብስን እና የከተማ ቀላል ባቡርን መጠቀም ይችላሉ:: የአገልግሎት ድግግሞሽን በተመለከተ አውቶቡሶቹ ቀኑን ሙሉ በምልልስ አገልግሎት የሚሰጡ ሲሆን ከጠዋት ጀምሮ እስከ ምሽት ድረስ አስተማማኝ አገልግሎት ይሰጣሉ። (Den Haag.com, 2023)

2.1.2. የግል የመጓጓዣ ዓይነቶች

ሀ/ የግል ብስክሌቶች

ሄግ ከተማ በኔዘርላንድ ውስጥ ካሉ ከተሞች መካከል በርካታ የብስክሌት ተጠቃሚዎች ያሉባት ከተማ እና ለሳይክል ተስማሚ መሰረተ ልማት የተሟላላት ከተማ ናት። የሄግ ከተማ ነዋሪዎች በጠንካራ የብስክሌት ባህላቸው ይታወቃሉ፣ ብዙ ነዋሪዎች ለዕለታዊ መጓጓዣ፣ ለመዝናኛ እና ለስራ የሳይክል ባለቤት ናቸው። በከተማዋ በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ የግል ብስክሌቶች እንደሚኖሩ ይገመታል።

ለሳይክል አሽከርካሪዎች ደህንነት እና ምቾት ቅድሚያ እንዲሰጡ ተደርገው የተሰሩት የብስክሌት መስመሮች ላይ የብስክሌት መንገድ መሆኑን የሚገልጹ ልዩ ልዩ ምልክቶች በቀለም የተሳለባቸው ሲሆን መስቀለኛ መንገዶች ላይ የሳይክል አሽከርካሪዎች የትራፊክ ሙቢራት ሲፈቅድላቸው ብቻ እንዲተላለፉ በማድረግ ቅንጅት ተፈጥሯል። ብስክሌት በዝቅተኛ ዋጋ፣ ከአየር ብክለት ነፃ የሆነ አገልግሎትን እና መኪና ሊይዘው ከሚችለው ስፍራ አነስተኛ ስፋት ያለውን ቦታ የሚይዝ ዘላቂ የሆነ የሞተር አልባ ትራንስፖርት ዓይነት ነው።



ፎቶ 33፡- በሄግ ከተማ የብስክሌት መሰረት ልማት በከፊል

እስከ ቅርብ ግዜ ወዲህ የአገራችን ከተሞች የብስክሌት መንገድ ለብቻው አልተሰራላቸውም ነበር። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በኮሪደር ልማት በርካታ ከተሞች የብስክሌት መስመሮችን እየዘረጉ ይገኛሉ።

ለሳይክል መንገድ ብቻ የተለዩ መስመሮች መዘርጋታቸው ደህንነቱ የተጠበቀ እና ምቹ ሁኔታን ለሳይክል ተጠቃሚዎች በመፍጠር አዳዲስ ተጠቃሚዎችን እንደሚያበረታታ ታምኖበታል። በሄግ የብስክሌት እንቅስቃሴ በተንቀሳቃሽ ምስል በምሳሌነት ለመመልከት የሚከተለውን የዩቲዩብ ሊንክ ይከፈቱ። https://www.youtube.com/watch?v=aMzWAoE1PDE&t=18s



ፎቶ 34፡- በሄግ ከተማ የብስክሌት መሰረት ልማት በከፊል

ደህንነቱ የተጠበቀ የብስክሌት ማቆሚያ ስፍራ (bike parking facilities) እና የብስክሌት መጋሪያ ጣቢያዎችን (bike-sharing stations) ጨምሮ ቡብስክሌት መሠረተ ልማት ላይ ሰፊ ስራዎች ተሰርተዋል።

በሄግ ነዋሪዎች የብስክሌት አጠቃቀም በተንቀሳቃሽ ምስል በምሳሌነት ለመመልከት የሚከተለውን የዩቲዩብ ሊንክ ይከፈቱ። https://www.youtube.com/watch?v=mkvetUjHtxwRw





ፎቶ 35፡- የብስክሌት ማቆሚያ ስፍራ እና የብስክሌት መጋሪያ ጣቢያ

በሄግ 370 ኪ.ሜ ርዝመት ያለው የብስክሌት መስመር ተሰርቶ አገልግሎት ላይ ውሏል። በሄግ የተሰሩት የብስክሌት መስመሮች በቀለም ምልክት የተደረገባቸው እና ከአረንጓዴ ቦታዎች ጋር የተናበቡና የተቀናጁ ሲሆኑ ይህም በከተማዋ አስደሳች የመንዳት ሁኔታን እንዲኖር አስተዋፅዖ አድርጓል። በከተማዋ ልዩ የብስክሌት መስመሮች መኖራቸው ሰዎች ደህንነታቸው ተጠብቆ ብስክሌት መንዳትን እንደ ዋና የመጓጓዣ ዘዴ እንዲመርጡ አበረታቷል።



ፎቶ 36፡- በሄግ የብስክሌት መስመር በከፊል

የብስክሌት ማቆሚያ ስፍራ

ዴን ሃግ ሴንትራል የባቡር ጣቢያ አቅራቢያ 8,500 ብስክሌቶችን ማስተናገድ የሚችል እሌኢ በ 2020 የተከፈተ ትልቅ የብስክሌት ማቆሚያ ስፍራ ይገኛል። የብስክሌት ማቆሚያ ጣቢያው 8,100 ካሬ ሜትር የሚሸፍን ሲሆን ከባቡር ጣቢያው ፊት ለፊት ከሚገኘው ምድር ቤት ውስጥ ይኛል። የመጀመሪያዎቹ 24 ሰዓታት የግል ብስክሌቶችን ለማቆም ክፍያ አይጠየቅም።

ለእያንዳንዱ ተጨማሪ 24 ለሊታት 1.25 ዩሮ ክፍያ ይከፈላል። (Bicycle Dutch, 2020; Den Haag, n.d.) ዴንሃግ ሆላንድስ ስፖር የባቡር ጣቢያ አቅራቢያ የሚገኘው የብስክሌት ማቆሚያ ስፍራም በተመሳሳይ ለመጀመሪያዎቹ 24 ሰዓታት የአገልግሎት ክፍያ አይጠይቅም። ከ24 ሰዓታት በኋላ ግን ተጠቃሚዎች በዴቢት ካርድ በመክፈል ወይም OV-chipkaartን በመጠቀም ለረጅም ጊዜ የአገልግሎት ክፍያ በመክፈል መጠቀም ይችላሉ። የክፍያ መጠኑም ከዴንሃግ ሴንትራል አቅራቢያ ከሚገኘው የብስክሌት ማቆሚያ ስፍራ ጋር ተመሳሳይ ነው። (NS, n.d.)

ባይሲክሌቴ (Biesieklette) በመባል የሚታወቀው ተቀጽም የብስክሌት ማቆሚያ ቦታዎችን በማስተዳደርና ጥቢቃ በማድረግ የሚታወቅ ተቋም ነው። የብስክሌት ማቆሚያ ጣቢያዎቹ የሚገኙባቸው ስፍራዎች በአውቶብስ እና በከተማ ቀላል ባቡር ፈርማታዎች እና በባቡር ጣቢያዎች አጠገብ ሊገኙ ይችኛሉ። ባይስክሌቴ የተባለው ተቋም የመጀመሪያዎቹ 24 ሰዓታት የግል ብስክሌቶችን ለማቆም ክፍያ አይጠየቅም። ለእያንዳንዱ ተጨማሪ 24 ለሊታት 0.5 ዩሮ ክፍያ ይከፈላል።

ጥቢቃ የማይደረግላቸው የብስክሌት ማቆሚያ ስፍራዎች በከተማው ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች ይኛሉ። ብስክሌተኞች ብስክሌታቸውን በሰንሰለት በሚገኙ የብስክሌት መደርደሪያዎች ጋር በሰንሰለት በማሰር አቁመው መሄድ ይችላሉ። እነዚህ የብስክሌት ማቆሚያ ስፍራዎች ጥቢቃ ባይኖራቸውም ለአጭር ጊዜ ብስክት በነጻ ለማቆሚነት እያገለገሉ ይገኛል። (Den Haag, n.d.)

ለ/ የእግር ጉዞ

የሄግ ተፈጥሮአዊ አቀማመጥ ለእግረኛ ምቹ ከተማ ያደርጋታል፤ ይህም ነዋሪዎች እና ጎብኚዎች በቀላሉ በእግር ተዘዋውረው ስራቸውን እንዲያከናውኑ እና እንዲጎበኙ ያስችላቸዋል። በሄግ የእግረኛ ብቻ መንገዶች ዲዛይን ለእግረኛ ደህንነት እና አካታችነት ቅድሚያ በመስጠት የተዘጋጁ ናቸው። በመንገድ ማቋረጫዎች ላይ ለእግረኞች ደህንነት የእግረኛ ማቋረጫ ዜብራዎች ጥቅም ላይ ውለዋል። ከተማዋ የእግረኛ መንገዶችን ወቅታዊ ጥገና በማድረግ ነዋሪዎች በእግራቸው እንዲጓዙ ታበረታታለች።

የእግረኛ መንገዶች ለከተማው ውበትን እንዲያጎናጽፉ ተደርገው መሰራታቸው ነዋሪዎች በእግር ለመንቀሳቀስ እንደ እንድ የጉዞ አማራጭ ሊጠቀሙ ይስተዋላል::

በሄግ በርካታ የእግረኛ-ብቻ ቦታዎች ይኖሩ፣ ግሮት ማርክስትራት (Grote Marktstraat) በመባል የሚታወቀው ዋና የገበያ አካባቢ ለእግረኛ ብቻ ተብሎ የተዘጋጀ መንገድ ይኖሩል:: ይህ ጎዳና ለእግረኛ ብቻ ተደርጎ የተሰራ ሲሆን ከሞተር ነክ ተሽከርካሪዎች ነፃ የሆነ ስፍራ ነው:: በሄግ ቢፓርኮች፣ በአረንጓዴ ቦታዎች፣ በመንገድ ዳርቻዎች የእግረኛ ብቻ መንገዶች ይኖሩሉ:: የእግረኛ መንገዶች ምልክት የተደረገባቸው ሲሆን እግረኞች በከተማው ውስጥ እንዲዟዙ ቀላል ያደርገዋል።



ፎቶ 37፡ በግሮት ማርክስትራት የመገበያያ ስፍራ የእግረኛ መንገድ

ሐ/ የግል መኪና

ከተማዋ የተሽከርካሪ እንቅስቃሴን የሚያቀላጥፍ የመኪና መንገዶች አሏት:: በከተማዋ ዙሪያ የቀለበት መንገድ የተሰራ ሲሆን ይህም የከተማውን ከፍለከተሞች እና በዙሪያዋ ካሉ አካባቢዎች ጋር በማገናኘት ሚናው ከፍተኛ ነው:: የመሬት ውስጥ የመኪና ማቆሚያ ስፍራዎች (underground parking facilities) በከተማው መሃል የሚገኙ ሲሆን አሽከርካሪዎች መኪናዎቻቸውን እንዲያቆሙ ያስችላል:: በከተማው ውስጥ ያለው የተለመደው የፍጥነት ገደብ 50 ኪ.ሜ በሰዓት ሲሆን የመኖሪያ አካባቢዎች ደግሞ በሰዓት 30 ኪ.ሜ. ነው:: (GPSmyCity,nd.)

በሄግ የግል መኪና ማሽከርከር በብዙ ፈተናዎች የታጀበ ነው። ውስን የመኪና ማቆሚያ ቦታ፣ የመኪና ማቆሚያ የአገልግሎት ክፍያ ከፍተኛ መሆኑ እና የመንገድ መዚጋጋት እንደ ችግር ተጠቃሽ ናቸው።

2.1.3. የጋራ ተንቀሳቃሽነት አማራጮች (Shared Mobility Options)

በሄግ ከተማ የብስክሌት መጋራት (bicycle-sharing)፣ ኢ-ሞፔድ መጋራት (e-moped-sharing)፣ የጭነት ብስክሌት መጋራት (cargo bike-sharing) እና የመኪና መጋራት አገልግሎቶችን (car-sharing services) ጨምሮ የተለያዩ የጋራ ተንቀሳቃሽነት አገልግሎት (shared mobility services) አማራጮች ይገኛሉ። እነዚህ የጋራ የመጓጓዣ ሞዴሎች ዘላቂነትን እና ምቾትን ያበረታታሉ።

እነዚህ አማራጮች የልዩ ልዩ ጉዞዎችን በማሳለጥ በመጓጓዣ አውታር ላይ የሚስተዋሉ ክፍተቶችን ይሞላሉ። ከተማው እነዚህን የህዝብ የጋራ አማራጮችን ከአጠቃላይ የትራንስፖርት ስትራቴጂ እና የመሰረተ ልማት ፕላኒንግ ጋር እንዲቀናጁ አድርጓል። ከዚህ በታች በሄግ የመጓጓዣ የመጋራት አገልግሎት ተሞክሮዎች በዝርዝር ቀርበዋል፦

ሀ/ የብስክሌት መጋራት አገልግሎት

በሄግ የብስክሌት መጋራት ጽንሰሃሳቡ ግለሰቦች ብስክሌቶችን በአነስተኛ ክራይ ወይም በውሰት ለአጭር ርቀት ጉዞ በመጠቀም እና በተዚጋጀላቸው ስፍራ በማቆም ቀጣይ ተጠቃሚዎች ላይከሎቹን እንዲገለገሉባቸው በማስብ በከተማ አስተዳደሩ የተዘረጋ ስርዓት ነው። ይህ አገልግሎት ተጠቃሚዎች በከተማው ውስጥ ከሚገኙ ከተለዩ የብስክሌት ማቆሚያ ጣቢያዎች ብስክሌቶችን እንዲከራዩ ያስችላቸዋል። የብስክሌት መጋራት በሄግ በባህሪው ተደራሽ፣ ዘላቂ እና ወጪ ቆጣቢ ነው። የሄግ የብስክሌት መጋራት ጽንሰሃሳብ እና ጥቅል መረጃ በተንቀሳቃሽ ምስል ለመመልከት የሚከተለውን የዩቲዩብ ሊንክ ይክፈቱ።

https://www.youtube.com/watch?v=ZrwO2haqaL8&t=273s

- **ተደራሽነት (Accessibility)**

ተደራሽነት ማለት ብስክሌቶች በተለያዩ ቦታዎች በኪራይ ይገኛሉ። ይህም ለተጠቃሚዎች እንደ አስፈላጊነቱ ብስክሌቶችን ወስዶ ለመጠቀም እና ለማቆም ምቹ ያደርገዋል። የብስክሌት መጋራት ስርዓት የስማርት ስልክ መተግበሪያዎችን የሚጠቀም ሲሆን ይህም የብስክሌት አገልግሎት ከፍያ ለመፈጸም እና ለመጠቀም ቀላል አድርጎታል። በሄግ ሁለት ዓይነት የብስክሌት መጋራት ስርዓቶች አሉ።

እነሱም ዶክድ እና ዶክለስ ስርዓት (Docked & Dockless System) በመባል ይታወቃሉ:: ዶክድ ስርዓት ተጠቃሚዎች ቴክኖሎጂ ከታገዘ የብስክሌት ማቆሚያ ጣቢያዎች ብስክሌቶችን ተከራይተው እንዲጠቀሙ እና በሲስተሙ ውስጥ ወዳለ ተመሳሳይ ጣቢያ እንዲመልሱ ያስችላቸዋል::

ዶክለስ ስርዓት ደግሞ የብስክሌት መጋራት ተጠቃሚዎች ስማርት ቴክኖሎጂን በመጠቀም ብስክሌቶችን ከማንኛውም ለዚሁ አገልግሎት ከተሰየመ ቦታ በመፈለግ በክራይ ወስደው መጠቀም እና ወደ ተመሳሳይ ስፍራ ማቆም እንዲችሉ ተደርጎ የተዘጋጀ ነው:: ብስክሌቶቹም ሆኑ ማቆሚያ ስፍራዎቹ ጂፒኤስ የተገጠመላቸው ስለሆኑ ተጠቃሚዎች በአቅራቢያቸው የሚገኙ ብስክሌቶችን እና ማቆሚያ ስፍራዎችን በሞባይል አፕልኬሽን ያሉበትን ስፍራ በመፈለግ መጠቀም ይችላሉ::

• ዘላቂነት (Sustainability)

በሄግ የብስክሌት መጋራት ዘላቂ የመጓጓዣ አማራጮችን በማበረታታት የትራፊክ መጨናነቅን ለመቀነስ፣ የካርቦን ልቀትን ለመቀነስ እና ጤናማ የአኗኗር ዘይቤዎችን ሰማስፈን አስተዋጽኦ አበርክቷል::

• ወጪ ቆጣቢነት

በሄግ የብስክሌት መጋራት ፕሮግራሞች የብስክሌት ባለቤት ከመሆን ወይም ታክሲዎችን በከፍያ ከመጠቀም በአገልግሎት ከፍያ ርካሽ እና ተመጣጣኝ በመሆናቸው በከተማው ነዋሪዎች ዘንድ ተመራጮች ናቸው:: ፕሮግራሞቹን የመንቀሳቀስ አማራጮችን ለማሻሻል እንዲረዳ ሄግ ከተማ ከህዝብ ማመላለሻ ስርዓቶች ጋር በማጣመር ተግባራዊ አድርጓል::

• በሄግ የብስክሌት መጋራት አገልግሎት ሰጪዎች

በሄግ የብስክሌት መጋራት አገልግሎት ሰጪዎች ሁለት ዓይነት ናቸው:: እነሱም የግል እና የመንግስት አገልግሎት ሰጪዎች ናቸው:: እንደ ዶንኪ ሪፐብሊክ እና ካርጎሮ (Donkey Republic and Cargoroo) ያሉ የግል ድርጅቶች ራሳቸውን ችለው የሚሰሩ ሲሆን ከሌላ ድርጅቶች ጋር በሽርክና የሚሰሩ እንደ ኤችቲኤም (HTM) ያሉ ድርጅቶችም አገልግሎት በመስጠት ይታወቃሉ:: የተለያዩ አይነት የአገልግሎት አቅራቢ ድርጅቶች መኖራቸው ለነዋሪዎች እና ለጎብኚዎች የሚያቀርቡትን የብስክሌት መጋራት አማራጮችን ተደራሽነት እና አማራጮችን ይጨምራል::

ዶንኪ ሪፐብሊክ እና ካርነሮ እና ጎ ሼሪንግ (Go Sharing) ያሉ የግል የብስክሌት መጋራት አገልግሎት አቅራቢዎች በገበያው ውስጥ ትልቅ ሚና የሚጫወቱ ሲሆን ለብስክሌት ኪራይ የሞባይል መተግበሪያን ይጠቀማሉ። ይህም ተጠቃሚዎች ብስክሌቶችን በተመቸ ሁኔታ እንዲያገኙ እና ቁልፋቸውን እንዲከፍቱ ያስችላቸዋል።

ከካርበን ልቀት ነጻ የሆኑ በኤሌክትሪክ የሚሰሩ አነስተኛ እና ቀላል፣ ተጠቃሚዎች ቆመው የሚያሽከረክሯቸው የሞተር ሳይክሎች ዝርያ የሆኑ (electric scooters) በአገልግሎት ሰጪቹ ቀርበዋል። በብስክሌት መጋራት የመንግስት ተሳትፎ ከህዝብ ማመላለሻ አካላት ጋር እንዲቀናጅ በማድረግ ሚናው ይገለጻል።

በሄግ ሁለቱም የግል እና ከመንግስት ጋር የተገናኙ የአገልግሎቱ አቅራቢዎች የትራፊክ መጨናነቅን መቀነስ እና የአየር ብክለትን መቀነስን የመሳሰሉ የጋራ አላማዎችን ይጋራሉ። የሄግ ማዘጋጃ ቤት የብስክሌት መጋራት ፕሮጀክቶችን እንደ ዘላቂ የከተማ ትራንስፖርት ስትራቴጂ በመውሰድ በዘርፉ ለተሰማሩ ድርጅቶች እየደገፈ ይኖራል። በዘርፉ የተሰማሩ ቦግል እና በመንግስት አካላት መካከል ያለው ትብብር በከተማ ውስጥ የብስክሌት መጋራት ስራዎችን አጠቃላይ ውጤታማነት ከፍ አድርጎታል።



ፎቶ 38፡- በሄግ የጋራ መገልገያ ብስክሌቶች እና ኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክሎች በከፊል



ፎቶ 39፡- በሄግ የጋራ መገልገያ ብስክሌቶች እና ኤልክትሪክ ሞተር ሳይክሎች በክፈል

- **የቁጥጥር ማዕቀፍ**

በሄግ የብስክሌት መጋራት ፕሮግራሞች ትግበራ እና አሠራር በከተማው ማዘጋጃ ቤት ደንቦች ይመራል። የብስክሌት መጋራት አገልግሎት ቡተለያዩ አቅራቢዎች የሚሰጥ ቢሆንም ሁሉም የብስክሌት መጋራት አገልግሎቶች በከተማ ውስጥ የካርበን ልቀትን በመቀነስ ለአየር ንብረት ለውጥ አወንታዊ አስተዋፅዖ ማድረጋቸውን ለማረጋገጥ የአየር ንብረት ፖሊሲዎችን ማክበር እንዳለባቸው ተደንግጓል። ስለ ስኩተር ቡተንቀሳቃሽ ምስል ለመመልከት የሚከተለውን የዩቲዩብ ሊንክ ይከፈቱ።

https://www.youtube.com/watch?v=sBCqAa0OGek&t=3s
https://www.youtube.com/watch?v=aL5MmDU2Ehg



ፎቶ 40፡- ኤሌክትኒክ-ስኩተር

ለ/ የጭነት ብስክሌት መጋራት አገልግሎት

በሄግ ውስጥ የጭነት ብስክሌት መጋራት አገልግሎቶች ለነዋሪዎች እና ጎብኝዎች ለአካባቢ ተስማሚ የሆነ የመጓጓዣ አማራጭ ናቸው፡፡ እነዚህ አገልግሎቶች በተለይ ኢቃዎችን ለማጓጓዝ፣ ከልጆች ጋር ለመጓዝ እና በመኪና ላይ ጥገኝነትን በመቀነስ ዘላቂ የከተማ እንቅስቃሴን ለማስፋፋት ጠቃሚ ናቸው፡፡ በሄግ የጭነት ብስክሌቶችን መጠቀም ብዙ ጥቅሞችን እየሰጠ ይገኛል፡፡

ተጠቃሚዎች የተሽከርካሪ ባለቤት መሆን ሳይጠበቅባቸው አገልግሎቱን በቀላሉ በክራይ የሚያገኙበት አማራጭ ነው፡፡ ይህም ለትራፊክ መጨናነቅ እና የካርቦን ልቀትን ለመቀነስ አስተዋፅኦ ያደርጋል። የጭነት ብስክሌቶች ተጠቃሚዎች ስለ ማቆሚያ ሳይጨነቁ ወደ መድረሻቸው እንዲጠጉ ያስችላቸዋል፡፡ በሄግ በርካታ ድርጅቶች የጭነት ብስክሌት መጋራት አገልግሎቶችን ይሰጣሉ፡፡ ከነዚህ መካከል ካርጎሮ እና ብላክ ባይክስ (Cargoroo and Black Bikes) ተጠቃሽ ናቸው፡፡



ፎቶ 41፡ በሄግ የሞኦት ብስክሌት

ሐ/ የኢ-ሞፔድ-መጋራት አገልግሎት

በሄግ ኢ-ሞፔድ-መጋራት ሌላው ታዋቂና ተወዳጅ አማራጭ ነው። የኤሌክትሪክ ሞፔዶች እካባቢ ስለማይበክሉ በነዳጅ ከሚሰሩ የሞተር ተሽከርካሪዎች ይልቅ ለሥነ-ምህዳር ተስማሚ ናቸው፡፡ ለኢ-ሞፔድ መጋራት አገልግሎት የሚውሉ ሞፔዶች ወይም ስኩተሮች ከመኪናዎች ይልቅ ወደ መድረሻዎች ሊጠጉ ስለሚችሉ የትራፊክ መጨናነቅን ለመቀነስ እና የመኪና ማቆሚያ ችግርን ይቀርፋሉ፡፡ የኢ-ሞፔድ መጋራት አገልግሎቶች ለተጠቃሚዎች በቀላሉ ተደራሽ እንዲሆኑ ተደርገው የቀረቡ ናቸው። ተጠቃሚዎች በአቅራቢያቸው የሚገኙ ስኩተሮችን በሞባይል መተግበሪያዎች መፈለግ ይችላሉ። በሄግ የኢ-ሞፔድ መጋራት አገልግሎት ዘላቂ እና የካርበን ልቀት የሌለው የትራንስፖርት አማራጭ ነው፡፡ አገልግሎቱ በግል መኪናዎች ላይ ጥገኝነትን በመቀነስ ለነዋሪዎችና ለንብኒዎች ተደራሽነትን አሻሽሏል፡፡



ፎቶ 42፡- ኢሞቲድ ተሽከርካሪ

መ/ የመኪና መጋራት አገልግሎት

በሄግ የመኪና መጋራት አገልግሎት የሚሰጡ በርካታ ድርጅቶች አሉ። ከነዚህም መካከል ግሪንዊልስ (Greenwheels)፣ ማይዊልስ (MyWheels) እና ስናፕካር (SnappCar) ያሉ አገልግሎት ሰጪች ተጠቃሾች ናቸው። ተጠቃሚዎች እንደ ጥና እና ኢንሹራንስ ያሉ ከመኪና ባለቤትነት ጋር ተያይዘው የሚወጡ ወጪዎች ሳይኖሩባቸው መኪናዎችን ለአጭር ጊዜ እንዲከራዩ ያስችላቸዋል። ይህ ዓይነቱ የመጓጓዣ አማራጭ አልፎ አልፎ ተሽከርካራ ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች ወሳኝ ነው። (Den Haag, n.d.)

ተጠቃሚዎች መኪናዎችን በሞባይል መተግበሪያዎች ፈልገው ማግኘት ይችላሉ። ለምሳሌ የግሪንዊልስ መተግበሪያ ደንበኞች መኪናዎችን ያለችግር እንዲከራዩ፣ በራቸውን ከፍተው እንዲገቡ እና ቆልፈው እንዲወጡ ያስችላቸዋል። (Greenwheels, n.d.) መኪና መጋራት ለስራ፣ ለመጓጓዣ ወይም ለመዝናኛ እንቅስቃሴዎች ምቹ አማራጭ ናቸው። በሄግ ለመኪና መጋራት አገልግሎት የተሰማሩ የተለያዩ ዓይነት ተሽከርካሪዎች አሉ። የአገልግሎቱ አቅራቢ ድርጅቶች ተጠቃሚዎች እንደየፍላጎታቸው ተስማሚ የሆኑ አማራጮችን እንዲመርጡ ለማስቻል ከአነስተኛ የከተማ መኪናዎች እስከ ትልልቅ የጭነት መኪናዎችን ለመኪና መጋራት አገልግሎት አቅርበዋል። (SIXT, n.d.)



ፎቶ 43፡- የመኪና መጋራት አገልግሎት

በሄግ የመኪና መጋራት አገልግሎት ዋጋ ተመጣጣኝ ሲሆን ተጠቃሚዎች ተሽከርካሪውን ለተጠቀሙበት ጊዜ ብቻ ተሰልቶ ይከፍላሉ። የአገልግሎት ክፍያ በያንስ ከ15 ደቂቃ ጀምሮ ነው። (Greenwheels, n.d.) ይህም ከመኪና ባለቤትነት ጋር ሲነፃፀር ለአጭር ጉዞዎች ወጪ ቆጣቢ ያደርገዋል።

የመኪና መጋራት በመንገድ ላይ ያሉትን ተሽከርካሪዎች ቁጥር በመቀነስ ለአየር ብክለት ቅነሳ አወንታዊ አስተዋፅዖ ያደርጋል። በሄግ ተጠቃሚዎች ከግል ተሽከርካሪዎች ይልቅ የመኪና መጋራትን ስለሚመርጡ የትራፊክ መጨናነቅ እና የካርቦን ልቀቶች ቀንሰዋል። የመኪና መጋራት አገልግሎቶች ለሁለቱም ነዋሪዎች እና ጎብኝዎች ምቹ የመጓጓዣ አማራጮች ናቸው። (Den Haag, n.d.)



ፎቶ 44፡- በሄግ የመኪና መጋራት አገልግሎት ተጠቃሚና የአገልግሎት ክፍያ መጠን

የመኪና መጋራት አገልግሎት እና የመኪና ኪራይ አገልግሎት የተለያዩ ናቸው። ለመኪና መጋራት አገልግሎት ጥቅም ላይ የሚውሉ መኪናዎች የሚከተሉት ባህሪያት አሏቸው፡-

- በማንኛውም ቀን እና በማንኛውም ሰዓት (24/7) በስማርት ሞባይል መተግበሪያ ወይም በአባነት ካርድ በኩል በቀላሉ ማግኘት ይቻላል።
- ተጠቀሚዎች ከ ሰዓት በፊት ማመልከት ይኖርባቸዋል።
- አገልግሎት የሚሰጡ መኪናዎች በሁሉም የከተማው አካባቢዎች ይኖሉ።
- ለአጭር ጉዞዎች ጥቅም ላይ ይውላል።
- ተጠቃሚዎች በደቂቃዎች ወይም በሰዓታት ላይ የተመሰረቱ ክፍያዎች ይከፍላሉ፤ ለአጭር ጉዞዎች ርካሽ ነው።

ለመኪና ኪራይ አገልግሎት የሚውሉ መኪናዎች የሚከተሉት ባህሪያት አሏቸው፡-

- በሥራ ሰዓት እና በስራ ቀን ብቻ ነው የሚገኙት።
- የዚህ አገልግሎት ተጠቃሚ ለመሆን ከቀናት በፊት ማመልከት ያስፈልጋል።
- መኪናዎቹ የተወሰኑ አካባቢዎች ወይም በአውሮፕላን ማረፊያ አካባቢ ይኖሉ።
- ረዘም ላለ ጊዜ ለሚቆይ ጉዞ ያለማላል።
- ተጠቃሚዎች በቀናት ወይም በሳምንታት ተሰልቶ ክፍያ ይፈጽማሉ፤

2.2. የተቀናጀ የመጓጓዣ አውታር (Integrated Transportation Network)

ሄግ የተናበበ እና የተቀናጀ የመጓጓዣ ስርዓት ተግባራዊ አድርጋለች። የሄግ የብስክሌት እና የእግረኛ መሠረተ ልማት ከሕዝብ ማመላለሻ ስርዓቱ ጋር (ባቡርን ጨምሮ) የተቀናጀ ነው። ይህም ተጠቃሚዎች ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ የትራንስፖርት ዓይነቶችን ለምሳሌ በእግር፣ በሳይክል፣ በአውቶብስ፣ በባቡር እና ቦግል ተሽከርካሪ ወዘተ በማጣመር በቅብብሎሽ የፈለጉበት ቦታ ለመድረስ ያስችላቸዋል። በከተማዋ የሚገኙ የመጓጓዣ አማራጮች አካል ጉዳተኞችን ጨምሮ ለሁሉም ተጠቃሚዎች ተደራሽ ናቸው።

በተለያዩ የመጓጓዣ ስልቶች መካከል እንከን የለሽ አገናኞች (seamless links) አሉ። ይህ በብስክሌት፣ በባቡር፣ በአውቶብስ መሳመሮች፣ በብስክሌት መጋሪያ ጣቢያዎች (bike-sharing stations) እና በእግረኛ መሳመሮች መካከል ምቹ የመተላለፊያ ነጥቦችን (transfer points) ያካትታል። መንገደኞች የብዝሃ ትራንስፖርት ጉዞዎችን (Multimodal Transports) ለምሳሌ ብስክሌት፣ አውቶብስ እና ባቡር ለመጠቀም የተቀናጀ ትኬት (integrated ticketing) መቁረጥ ይችላሉ።

የሄግ የተቀናጀ ትኬት ስርዓት የሚከተሉትን ያካትታል፦

• እቪ- ቺፕካርት (OV-Chipkaart)፦ እቪ- ቺፕካርት በሄግ ለህዝብ ማመላለሻ የመክፈያ ዘዴ ሆኖ የሚያገለግል ንክኪ የሌለው ስማርት ካርድ (contactless smart card) ሲሆን ቀደም ሲል የነበረውን የወረቀት ትኬቶችን ያስቀረ ነው። ተሳፋሪዎች በአውቶቡሶች፣ በባቡሮች እና በሌሎች የመጓጓዣ አማራጮች ውስጥ በሚገቡበት እና በሚወጡበት ጊዜ በአካል ክፍያ የሚፈጽሙበት ስማርት ካርድ ነው።

እቪ- ቺፕካርት በኔዘርላንድ መንግሥት እና በሕዝብ ማመላለሻ አቅራቢዎች የሚተዳደር አገር አቀፍ ሥርዓት ነው። ሶስት ዋና ዋና የእቪ- ቺፕካርት ዓይነቶች አሉ። እነሱም ለአንድ ጊዜ ብቻ ወይም ለአንድ ቀን ብቻ የሚገለግል እና የሚወገድ ካርድ፣ ስም የሌለው ለተበኝዎች የሚዘጋጅ ካርድ እና ለኔዘርላንድ/ቤልጂየም/ጀርመን ነዋሪዎች በግል ተመዝግበው የሚሰጡ ካርዶች ናቸው።



ፎቶ 45፦ እቪ- ቺፕካርት

• የተቀናጀ የመጓጓዣ ታሪፍ ስርዓት (Integrated Fare System)፦

እቪ- ቺፕካርት በሄግ ሜትሮፖሊታን አካባቢ በሚገኙ የሚንቀሳቀሱ አውቶቡሶች፣ ባቡሮች እና ሌሎች የህዝብ ማመላለሻ አገልግሎቶችን ለመክፈል ያገለግላል። የተቀናጀ የመጓጓዣ ታሪፍ ስርዓት በአንድ ከተማ ወይም ክልል ውስጥ ያለ የክፍያ እና በብዙ የመጓጓዣ ዘዴዎች የሚተላለፉትን አጠቃላይ ማዕቀፎች እና ስልቶችን ያካትታል። የተቀናጀ የመጓጓዣ ታሪፍ ስርዓት እቪ- ቺፕካርትን ብቻ ሳይሆን እንደ ሞባይል መተግበሪያዎች ያሉ ሌሎች የክፍያ አማራጮችን እንዲሁም የጉዞ እቅድ

ያሉ ተጨማሪ አገልግሎቶችን ያጠቃልላል። አቪ- ቺፕካርት አካላዊ የመጓጓዣ ታሪፍ መክፈያ ካርድ ሲሆን የተቀናጀ የመጓጓዣ ታሪፍ ስርዓት ደግሞ አቪ-ቺፕካርትን እና ሌሎች አካላትን ያካተተ ሰፊ ግዕቀፍ ነው። የተቀናጀ የመጓጓዣ ታሪፍ ስርዓት ከከፍያ ባለፈ የጉዞ እቅድ ለማቀድ ያስችላል።

• እንከን የለሽ ዝውውሮች (Seamless Transfers)፦ ተጓዦች በተለያዩ የህዝብ ማመላለሻ መንገዶች (ለምሳሌ ከአውቶቡስ ወደ ባቡር) ሲያዋወሩ፣ አዲስ ትኬት መግዛት ሳያስፈልጋቸው አቪ- ቺፕካርትን በመጠቀም ዝውውር እንዲያደርጉ ያስችላቸዋል።

• የመጓጓዣ ታሪፍ ከፍያ (Fare Capping)፦ የአቪ- ቺፕካርት ስርዓት ተጓዦች የቱንም ያህል ጉዞ ቢያደርጉም ከአለት ወይም ከለምንታዊ ከፍተኛ ከፍያ በላይ እንዳይከፍሉ የሚያስችል የታሪፍ ከፍያ ዘዴ አማራጭ ነው።

• የጉዞ እቅድ ማውጣት (Journey Planning)፦ በሄግ በእንላይን እና በሞባይል አፕሊኬሽኖች አማካይነት ነዋሪዎች አቪ- ቺፕካርትን በመጠቀም የመልቲሞዳል ጉዞዎችን እንዲያቅዱ የሚያስችል የተቀናጀ የጉዞ እቅድ ስርአት ተግባራዊ ተደርጓል። ይህ ስርአት የመጓጓዣ መርሃ ግብሮችን፣ የመነሀድ አማራጮችን እና የታሪፍ መረጃን በተቀናጀ መልኩ ያሳያል። ደምበኞች ባለው የትራፊክ ሁኔታ ወይም የጉዞ መዘግየቶች ላይ ተመስርተው ለአገልግሎት አቅራቢዎች ጥቆማዎችን እና አስተያየቶችን የሚሰጡበት ስርዓት ተዘርግቷል።

• ተደራሽነት፦ አቪ- ቺፕካርት ነዋሪዎችና ጎብኚዎች በቀላሉ ማግኘት የሚችሉ ሲሆን ይህም የህዝብ ማመላለሻ ስርዓቱን የበለጠ ተደራሽ እና ለተጠቃሚዎች ምቹ ያደርገዋል።

ይህ በሄግ ያለው የተሰመደ የቲኬት አከፋፈል ስርዓት ተጓዦች በተለያዩ የመጓጓዣ መንገዶች አንድ የመክፈያ ዘዴን እንዲጠቀሙ በማድረግ እንከን የለሽ የመልቲሞዳል ጉዞዎችን ያስችላል። አጠቃላይ የተጠቃሚውን ልምድ ያሳድጋል፣ ነዋሪዎች እና ጎበኝዎች የህዝብ መጓጓዣን እንዲጠቀሙ ያበረታታል።

የአቪ- ቺፕካርት ከሄግ ከተማ የመጓጓዣ ስርአት ጋር እንዲቀናጅ መደረጉ የተቀናጀ ትኬት በከተማ ውስጥ እንዴት የመልቲሞዳል ጉዞን እንደሚያመቻቹ እና እንደሚያበረታቱ አይነተኛ ምሳሌ ነው። የሄግ ከተማ የዘርፉ ባለሙያዎች ለህብረተሰቡ ስለመልቲሞዳል ትራንስፖርት አገልግሎት የማንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርዊ ፕሮግራሞችን ተግባራዊ አድርገዋል፤ እያደረጉም ይገኛሉ። ነዋሪዎች የግል መኪና ከመጠቀም እንዲቆጠቡ እና የህዝብ ትራንስፖርቶችን እንዲጠቀሙ ሰፊ ስራዎች ተሰርተዋል።

ከተማ አስተዳደሩ የመልቲሞዳል መጓጓዣን የሚደግፉ ፖሊሲዎችን እና አገልግሎቶችን ተግባራዊ ለማድረግ ከአሰሪ ተቋማት ጋር ምክክር አድርጓል።



ፎቶ 46፡- የከተማ ትራንስፖርት አማራጮች በከፊል

ክፍል 3፡- የተወሰዱ ዋና ዋና ትምህርቶች

በአገራችን የከተሞች ትራንስፖርት ዘርፍ ከግንዛቤ ዕጦትና ትኩረት ማነስ የተነሳ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ አድጉቱ አዝጋሚ ሆኖ ቆይቷል። ስለሆነም ይህን ሁኔታ ለማሻሻል ትብብር መድረኩ ከኔዘርላንድ ሄግ ከተማ በዘላቂ ትራንስፖርት አገልግሎት ስራዎች ተገቢ ተሞክሮ ወስዷል።

ሄግ የዘርፉን ስራዎች በተቀናጀ መልኩ ለመምራትና ለመፈጸም የተለያዩ የህግ ማዕቀፍና ፖሊሲ በአገር አቀፍ ደረጃ ነድፈው ያለመሸራረፍ ተግባራዊ ማድረጋቸው፣ ስራውን ለማስፈጸም የሚያግዝ ተቋማዊ አደረጃጀትና መስተጋብር መፍጠራቸው፣ በተግባር ደረጃ ከፖሊሲና ስትራቴጂዎቻቸው በመመንዘር ወደ ተጨባጩ ስራ ሊያስገቡዋቸው የሚያስችሉ ቴክኒካዊ መመሪያዎችንና ጋይድ ላይኖችን አዘጋጅተው ሙተግበራቸው እና ለስራዎቹ መሳካት የፖለቲካ አመራሩ ያሳየው ቁርጠኝነት እንደ መልካም ተሞክሮ ተወስዷል። ከዚህ በተጨማሪም የሚከተሉት እንደ ትምህርት ተወስደዋል፡-

- ዜጎችን በተለያዩ የህዝብ አስተዳደር እና ውሳኔ አሰጣጥ ውስጥ ማሳተፍ ሁሉ አቀፍነትን ያጎለብታል፣ አገልግሎቶች የተለያዩ የህዝብ ፍላጎቶችን የሚያሟሉ መሆኑን ማረጋገጡ፣
- የህብረተሰቡን በከተማ ፕላን እና በውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች ማሳተፍ መቻሉ እና ውጤት ማስመዝገቡ፣
- ያልተማከለ የአስተዳደር ስርአት በየደረጃው ለሚቀርቡ ማዘጋጃቢታዊ እና መንግስታዊ አገልግሎቶች ለማቅረብ፣ ለመከታተል፣ ለመገምገም እና ለመወሰን ምቹ ሁኔታን መፍጠሩ፣
- ከተሞች ገቢያቸውን እሚጠው እንዲሰበስቡና እንዲያስተዳድሩ ማበረታታትና መፍቀድ ለህብረተሰቡ የአገልግሎት ፍላጎቶች ቀልጣፋ ምላሽ መስጠትን ማሳደጉ፣
- የከተማዋን የኑሰም አቀፋዊነት ደረጃ ለኢኮኖሚ ልማት እና ለባህል ማንልበት ወሳኝ መሆኑ ትምህርት ተወስዷል፣
- ከተሞች ቱሪዝምን እንደ አንድ የኢኮኖሚ ዘርፍ በመውሰድ መስህቦችና ባህላዊ ቦታዎችን ተገቢውን በጀት በመመደብ እንዲለሙ ማድረግ እንዳለባቸው ትምህርት ተወስዷል። ቱሪዝም የስራ እድል ፈጠራን ያበረታታል።
- እንደ ማዱሮዳም እና ሼቨኒንገን የመሳሰሉ የባህር ዳርቻዎችና መዝናኛ ስፍራዎች ቱሪዝምን በማበረታታት ለከተሞች ገቢ አስተዋጽኦ ማድረጋቸው፣

- ለማህበራዊ አካታችነት እና ለብዝሃነት ትኩረት መሰጠቱ፤
- ብዙ የመጓጓዣ ዘዴዎችን (የከተማ ቀላል ባቡር፣ አውቶብስ፣ ታክሲ፣ ሳይክል ወዘተ) የሚያጣምር የተቀናጀ የከተማ ትራንስፖርት ሥርዓት ተግባራዊ መደረጉ የመንገድ መዘጋጋትን መቀነሱ፣ የከተማ እንቅስቃሴን በእጅጉ ማቀላጠፉ፣
- የብስክሌት ልዩ መስመሮችን እና የብስክሌት ማቆሚያ ቦታዎችን ማዘጋጀት ህብረተሰቡ ብስክሌትን እንዲጠቀም ከማበረታታት ባለፈ የበለጠ ዘላቂ እና ጤናማ የከተማ አካባቢን ማምጣት መቻሉ፤
- ለአካባቢ ተስማሚ የሆኑ የትራንስፖርት አማራጮች (በዋናነት የኤሌክትሪክ አውቶቡሶች እና የጭነት ብስክሌቶች) ቅድሚያ መሰጠት እንደሚገባ፤ ይህም የካርቦን ልቀትን ለመቀነስ እና አረንጓዴ ከተማን ለመፍጠር አስተዋፅኦ ማድረጉ፤
- ለአረንጓዴ መሠረተ ልማት እና ለዘላቂ የከተማ ልማት ትኩረት መሰጠቱ፤
- የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ እና መልሶ መጠቀም ስራዎች የአካባቢን ዘላቂነት እና የህዝብ ጤና እንዲጠበቅ መደረጉ፤
- የህብረተሰቡን ግንዛቤ ለማሳደግ የህዝብ ትራንስፖርት አጠቃቀም እና የአካባቢ ጥበቃን በተመለከተ ትምህርታዊ ፕሮግራሞች ተግባራዊ መደረጋቸው፤

የተመለደው የከተማ ዘላቂ ትራንስፖርት መልካም ተሞክሮም ከሀገራችን የከተሞች ትራንስፖርት እገልግሎት ጋር ተጣጥሞ የአፈጻጸም ስትራቴጂ እንዲያመላክት ተደርጎ ተዘጋጅቷል። በመሆኑም በመላ የሀገራችን ከተሞች በተጠቀሱት መሰረታዊ ጉዳዮች ላይ በትኩረት እንዲሰሩ የሚያስችላቸውን ተግባራዊ እንቅስቃሴ ውስጥ መግባት ለነገ ሊባል የማይችልና በአጣዳፊ ሁኔታ ሊገባበት የሚገባ ጉዳይ ነው።

ማጣቀሻዎች

Bike-sharing and e-moped-sharing in The Hague (2024). The Hague. Available at: https://www.denhaag.nl/en/getting-there-and-around/cycling/bike-sharing-and-e-moped-sharing-in-the-hague/

Bicycle Dutch (2013). 'Riding in the Hague' BICYCLE DUTCH. Available at: https://bicycledutch.wordpress.com/2013/01/24/riding-in-the-hague/

Bicycle Dutch (2019). 'Bike share the Dutch way' BICYCLE DUTCH. Available at: https://bicycledutch.wordpress.com/2011/03/17/bike-share-the-dutch-way/.

Bicycle Dutch (2020). 'A huge new bicycle parking garage in The Hague'. Available at: https://bicycledutch.wordpress.com/2020/07/01/a-huge-new-bicycle-parking-garage-in-the-hague/

CBS (2023). 'StatLine - Unemployment rates by municipality'. Available at: https://www.cbs.nl/en-gb

CILC (2023) 'About CILC'. Available at: https://www.cilc.nl/about-cilc/

Cycling routes The Hague | DenHaag.com (2024). denhaag.com. Available at: https://denhaag.com/en/cycling

Den Haag (n.d.) 'Car sharing - The Hague'. Available at: https://www.denhaag.nl/en/nature-and-environment/car-sharing/

Den Haag (n.d.) 'Parking your bike safely in The Hague'. Available at: https://www.denhaag.nl/en/getting-there-and-around/cycling/parking-your-bike-safely-in-the-hague

Den Haag.com (2023) 'Public transport in The Hague'. Available at: https://denhaag.com/en/bereikbaarheid-en-vervoer/openbaar-vervoer-den-haag

DenHaag.com (2024) 'Cycling routes The Hague'. Available at: https://denhaag.com/en/cycling

Delaneykrftwrk.ca (2022). 'Joyride and HTM launch bike share in The Hague, expanding public transit offering - Joyride'. Available at: https://joyride.city/blog/joyride-and-htm-launch-bike-share-in-the-hague-expanding-public-transit-offering-html/.

Dutch Railway Museum (n.d.) Available at: https://www.spoorwegmuseum.nl

European Commission (2022). 'Green Urban Spaces and Sustainable Development': The Case of The Hague. Available at: https://ec.europa.eu/environment/green-urban-spaces.htm.

EURES (2023). 'Labour market information: Netherlands'. Available at: https://eures.europa.eu/living-and-working/labour-market-information/labour-market-information-netherlands_en.

Eurostat (2023) 'Population on January 1st by age group and sex'

Gemeente Den Haag (2023). 'Economic overview and statistics'. Available at: https://www.denhaag.nl/en.

Gemeente Den Haag (2024). 'Urban Mobility Plan: Enhancing Sustainable Transport in The Hague'. Available at: https://www.denhaag.nl/en/urban-mobility-plan.htm.

Greenwheels (n.d.). 'Rent a shared car in The Hague'. Available at: https://www.greenwheels.nl/en-us/rent-a-car/the-hague.

Hague City International Relation Department (2024) 'City of the Hague' Presentation to Ethiopian Cities Association Delegation

Hilary Staples (2024). 'Holland-Cycling.com - Day trips'. Available at: https://www.holland-cycling.com/the-hague/where-to-go-the-hague/day-trips-the-hague.

HTM (n.d.). 'Our transport'. Available at: https://www.htm.nl/en/about-htm/our-transport.

HTM (n.d.) 'Tram History'. Available at: https://www.htm.nl

HTM Personenvervoer (n.d.). 'About HTM'. Available at: https://www.htm.nl/en/about-htm/our-transport/.

Joyride (2022) 'Joyride and HTM launch bike share in The Hague, expanding public transit offering'. Available at: https://joyride.city/blog/joyride-and-htm-launch-bike-share-in-the-hague-expanding-public-transit-offering-html/

Madurodam (2023). 'Discover Holland's highlights and heritage'. Available at: https://www.madurodam.nl/en.

Municipality of The Hague (2023) 'Economic impact survey'. Available at: https://www.denhaag.nl/en

Netherlands Institute for Transport Policy Analysis (2023). 'Bicycle Infrastructure in Dutch Cities'. Available at: https://www.kimnet.nl/publications/bicycle-infrastructure.htm.

Netherlands Tourism (2023). 'Madurodam – A Miniature Park Worth Visiting'. Available at: https://www.netherlands-tourism.com/madurodam-a-miniature-park-worth-visiting/.

NS (n.d.). 'Secure bicycle storage facilities'. Available at: https://www.ns.nl/en/bicycle-storage/guarded-bicycle-storage-with-attendants.html.

OECD iLibrary (2023) 'Development Co-operation Profiles – Netherlands'. Available at: https://www.oecd-ilibrary.org/sites/2faea623-en/index.html

RE:BORN Real Estate (2024). 'The Pier - RE:BORN Real Estate'. Available at: https://re-born.com/en/projecten/the-pier/.

SIXT (n.d.) 'Car sharing The Hague'. Available at: https://www.sixt.com/share/car-sharing/the-hague/

The Hague (2024) 'Bike-sharing and e-moped-sharing in The Hague'. Available at: https://www.denhaag.nl/en/getting-there-and-around/cycling/bike-sharing-and-e-moped-sharing-in-the-hague/

The Hague International Centre (2023). 'Economic sectors'. Available at: https://www.thehagueinternationalcentre.nl/economic-sectors.

The Hague International Centre (2023). 'Peace and Justice | The Hague International Centre'. Available at: https://www.thehagueinternationalcentre.nl/relocating/why-the-hague-region/work-in-the-netherlands/work-in-the-hague-region/peace-and-justice.

The Hague Marketing Bureau (2023). Sustainable Tourism and Urban Planning in The Hague. Available at: https://www.thehague.com/sustainable-tourism.htm.

The Hague Municipal Council (2023). 'The Hague Municipal Council' Available at: https://www.denhaag.nl/en/municipal-council/the-hague-municipal-council/.

The Hague Municipal Organisation (2023). 'The municipal organisation' Available at: https://www.denhaag.nl/en/municipal-organisation/the-municipal-organisation/.

The Hague University of Applied Sciences (2023). 'Student life in The Hague'. Available at: https://www.thuas.com/study-choice/student-life/student-life-hague-delft-and-zoetermeer.

Wikipedia (2023). 'Peace Palace' - Wikipedia. Available at: https://en.wikipedia.org/wiki/The_Hague,_Netherlands.

Wikipedia (2023). 'The Hague'. Available at: https://en.wikipedia.org/wiki/The_Hague,_Netherlands.

Wikipedia (n.d.). 'Trams in The Hague'. Available at: https://en.wikipedia.org/wiki/Trams_in_The_Hague.

ዕዝል፡- ልዩ ልዩ የብስክሌት ዲዛይኖች እና የብስክሌት ክፍል ስያሜዎች





Cities Development for better Life!




የከተሞች
ለተሻለ ህይወት!



Cities Development for Better Life!

የከተሞች ልማት ለተሻለ ህይወት

www.ethiopiancities.org

STRATEGIC PRIORITIES OF ECA

- Capacity building and Service provision to member cities (offering platform for knowledge exchange, tailored training, advisory service, documentation & information exchange);
- Lobby and Advocacy for the interests of Member Cities;
- Representation, networking and partnership.

ECA SOCIAL MEDIA

https://www.facebook.com/Ethiopian-Cities-Association-363331527583292

https://www.facebook.com/ketema.zelalem.37

Ethiopian Cities Association ECA

https://www.linkedin.com/in/yeketemoch-medrek-ethiopian-cities-association-a32963230/

https://twitter.com/CitiesEthiopian

www.ethiopiancities.org

https://www.flickr.com/photos/197278555@N08/

http://www.youtube.com/@ethiopiancitiesassociation8644

ECA ADDRESS

የትብብር መድረኩ አድራሻ

Tel: +251115576055
Fax: +251115576088
P.O.Box: 40960
E-mail: ethiopiancities2011@gmail.com
www.ethiopiancities.org
አዲስ አባባ፣ ኢትዮጵያ
ሜክሲኮ አደባባይ ኮሜርስ ፊትለፊት ህብረት ባንክ ዋና መ/ቤት ህንጻ 4ተኛ ፎቅ